በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት የሚገነቡ ግንባታዎች እና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደር ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2006 ዓ/ም

አዲስ አበባ

የምህፃረ-ቃል ፍች /ACRONYM/ IV

ክፍል አንድ 1

- *መግቢያ* 1
- የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር 2
- የድርጅቱ ስልጣንና ተግባር 2
- የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት 3

ድርጅታዊ መዋቅር 3

የሰው ኃይል 4

- የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ 4
- የኦዲቱ ዓላማ 4
- የኦዲት ትኩረቱ አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) 5
- የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት (AUDIT EVALUATIVE CRIERIA) 5
- የዝርዝር ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 5

ክፍል ሁለት 7

ግኝቶች 7

አዋጅ ደንብና መመሪያ በተመለከተ፣ 7

ድርጅቱ የተሟላ የሰው ሃይልና አደረጃጀት ያለው መሆኑን በተመለከተ ፣ 9

ኤርፖርቶች ለመገንባት በቅድሚያ የሚደረግ የአዋጪነት ጥናት ስለመኖሩ በተመለከተ፣ 10

አብዛኞቹ የድርጅቱ ኤርፖርቶች ፣የይዞታ ካርታ፣ የመሬት አጠቃቀም ካርታ እና መሪ ዕቅድ /Master Plan/ የሌላቸው መሆኑን በተመለከተ፣ 11

የድርጅቱ ግንባታዎች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ እና የኮንትራክት ዋጋ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ 12

የተጠናቀቁ ግንባታዎች ርክክብ እና በተገባላቸው ውል መሠረት ስለመሰራታቸውና በታዩ ግድፈቶች ላይ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፣ 14

ኤርፖርቶች አስተማማኝ ደህንነት ያላቸውና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን በተመለከተ 15

የድርጅቱ ግንባታዎች ደረጃቸውን የጠበቁና በውሉ መሰረት እየተገነቡ መሆናቸውን በተመለከተ፡- 20

ድርጅቱ የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድርበት ወቅት ያነሰ ዋጋ ብቻ መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ 29

በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች/ ህንፃዎች/ የውሃ አቅርቦት እና አሳንሱር በተመለከተ 30

በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት በግንባታው ውል መሰረት ስራዎቹ ሙሉ በሙሉ ስለመሰራታቸው በሚመለከተው ባለ ሞያ ማረጋገጫ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ 31

ግንባታቸው የተጠናቀቁ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ መሰረተ ልማቶች ስርአትና፣ ቀጣይነት ባለው መንገድ፣ ጥገናና እድሳት እየተደረገላቸው መሆኑን በተመለከተ 32

- ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን በተመለከተ 34

ድርጅቱ ያከራያቸው የኪራይ ቦታዎች በመመሪያው መሰረት የተቀመጠላቸው የኪራይ የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ድጋሚ ለጨራታ የሚቀርቡ ስለመሆናቸው በተመለከተ 34

ድርጅቱ የኪራይ ውሉ ዘመን ሲያበቃ ተከራይ በኪራይ የተረከበውን ባዶ ቦታ ወድያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንዲመልስና እንዲያስረክብ መደረጉን በተመለከተ 36

ተከራይ የኪራይ ውሉ ሳያከብር ሲቀር በመመሪያው መሰረት ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉን እንዲቋረጥ ስለመደረጉ በተመለከተ........ 36

በጨረታ መከራየት ያለባቸው የድርጅቱ የኪራይ ቦታዎች የጨረታ ህጉን ተከትለው እየተከራዩ ስለመሆናቸው በተመለከተ 37

በክልል ኤርፖርቶች በድርድር የሚከራዩ ቦታዎች በመመሪያው መሰረት የድርድር ኮሚቴው ቦታው ለተከራዩ ከማስረከቡ በፊት ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ ማስፀደቁን በተመለከተ 41

ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች ጥናት በማድረግ በየአመቱ ተመጣጣኝ ኪራይ ጭማሪ እየተደረገ ስለመሆኑ በተመለከተ 41

ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውልን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ 42

ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ 44

ክፍል ሦስት........ 47

የመደምደሚያ ሀሳቦች........ 47

ክፍል አራት 50

ማሻሻያ ሀሳቦች 50

አባሪዎች........ 55

አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA)........ 55

አባሪ 2፡ በጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ በተመለከተ .... - 58 -

አባሪ 3፡ ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን በተመለከተ .... - 59 -

አባሪ 4፡ ያለ ክፍያ ተከራዮች በተርሚናል አንድ እና ሁለት የሚጠቀሙበት የድርጅቱ ቦታ........- 61 -

የምህፃረ-ቃል ፍች /ACRONYM/

ICAO: International Civil Aviation Organization.

FAA: Federal Aviation Organization.

EDS: Explosive Detection System.

VIP: Very Important Person.

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በሀገሪቱ ጥራት ያለው የኤርፖርት መሠረተ ልማትና አገልግሎት ለመስጠት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 82/1995 ጥር 16 ቀን 1995 ዓ.ም የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው።
2. ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የኤርፖርት መሠረተ ልማትን የማስፋፋትና የማሻሻል፤ የሚሰጡ የኤርፖርት አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ቀልጣፋ፣ ብቃት ያላቸው፣ ተገልጋይ ተኮር እና ደህንነታቸው የተጠበቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነው።
3. የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በአሁኑ ወቅት አስራ ሰባት ኤርፖርቶችን በማስተዳደር ላይ ሲሆን፣ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ የኤርፖርቶችን ቁጥር 21 ለማድረስ በያዘው ዕቅድ መሠረት ሌሎች ኤርፖርቶችን በመገንባት፤ በማሻሻልና በማስፋፋት፤ እንዲሁም በሀገሪቱ የሚገኙ አንዳንድ የአውሮፕላን ማረፊያ ጥርጊያ ሜዳዎችን (airstrips) በስሩ አድርጎ ለማስተዳደር እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡
4. በድርጅቱ መዋቅር ስር ከሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች አንዱ የኤርፖርት መሠረተ ልማት ዳይሬክቶሬት ሲሆን ቀደም ሲል በኤርፖርት ምህንድስና መምሪያ ደረጃ ተዋቅሮ በሁለት ዋና ክፍል ማለትም ኤርፖርት ምህንድስና ዋና ክፍል እና በኮንስትራክሽንና ኢንስታሌሽን በተባሉ ዋና ክፍሎች ተደራጅቶ ልዩ ልዩ የኤርፖርት መሠረተ ልማት ግንባታዎችና የማስፋፊያ ሥራዎች ሲያስተዳደር የነበረ ሲሆን፣ አዲስ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት /BPR/ ተጠንቶ የሙከራ ትግበራ ከተጀመረ በኋላም በዳይሬክቶሬት ደረጃ በምህንድስና ለዲዛይንና ኮንስትራክሽን እንዲሁም በፕላንና ስታንዳርድ በሚባሉ ሁለት ቡድኖች ተደራጅቶ ከመስከረም 2003 ዓ.ም ጀምሮ ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች እያከናወነ ይገኛል።
5. መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ተነጥሎ በደንብ ከተቋቋመ በኋላ ላለፉት አስር ዓመታት ልዩ ልዩ የካፒታል ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለአገልግሎት ያዋለ ሲሆን፣ በአሁኑም ሰዓት በርካታ ፕሮጀክቶች በግንባታ ላይ ናቸው። ቢሆንም አብዛኞቹ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት የማይጠናቀቁ ከመሆናቸውም ባሻገር የድርጅቱ የስራ ሃላፊዎች ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን እርማጃ በመውሰድ ላይ አናሳ ነው፡፡
6. በተጨማሪ ድርጅቱ ሁለት ዓይነት የገቢ ምንጮች ያሉት ሲሆን እነሱም፡- አንደኛው ኤሮኔቲካል የሆኑ ገቢዎች ሲሆኑ ማለትም ከአውሮፕላን ንግድና እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ሆነው የክፍያ ታሪፍ በመንግስት እየፀደቀ በኢትዮጳያ ኤሮኔቲካል መረጃ /AIP-ETHIOPIA/ ውስጥ ታሪፍ ተገልጾ ሁሉም አብራሪዎች በእኩልነት የሚተዳደሩበት ሲሆን ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ደግሞ ከአውሮፕላን ንግድ ሥራ ላይ ከተሰማሩበት በተጨማሪ የነፃ ገበያ ህብረተሰብ በኤርፖቶች አካባቢ ለአውሮፕላኖች እንቅስቃሴ፣ ለመንገደኞች እና ለካርጎ ማጓጓዣ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ የንግድ

ተቋማት በመክፈት አገልግሎት ከሚሰጡ ከኪራይ አገልግሎት የሚገኝ ገቢ ሲሆን ድርጅቱ ከዚህ የሚገኘውን ገቢ ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥናት በማድረግ ለማሳደግ የሚያደርገውን ጥረት አናሳ መሆኑና ይህን የገቢ ምንጭ ለማስተዳደር በ1999 ዓ/ም ያወጣውን መመሪያ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ አናሳ ነው፡፡

የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር

7. የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 25/1984 መሠረት ነው፡፡ ከተሰጠውም ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-
   - የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፤ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፤
   - ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር ምደባና ስንብት ደመወዝና አበል ያፀድቃል፣
   - የድርጅቱን የስራ ፕሮግራም በጀትና የውስጥ ደንብ ያጸድቃል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣
   - የድርጅቱን የረጅም ጊዜ ብድሮች ያፀድቃል፣
   - በድርጅቱ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፣
   - የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያመላክታል፣
   - በድርጅቱ የሚመነጩ አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ያፀድቃል፣
   - በድርጅቱ የሚከናወኑና የበላይ አመራሩን ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣
   - ድርጅቱን በመወከል ከሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

የድርጅቱ ስልጣንና ተግባር

8. ድርጅቱ የተጣለበትን የስራ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባሮች አሉት፤ እነዚህ የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባሮች ድርጅቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 82/1995 ጥር 16 ቀን 1995 ዓ.ም ሲቋቋም በአዋጅ ቁጥር 111/1969 ለቀድሞ የአየር ትራንስፖርት ባለስልጣን ተሰጥተውት የነበሩ መብትና ግዴታዎች ለድርጅቱ መተላለፋቸውን በደንቡ ተራ ቁጥር 9 ተቀምጧል፡፡ **/ ስለዚህ ከዚህ በኋላ ባለስልጣኑ የሚለው ድርጅቱ በሚል ታሳቢ ይደረግ/**
   - የአየር መንገዶችና ጠቅላላ የአይሮፕላን አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ(ታሪፍ) ለማስወሰንና የማስፈጸም፤
   - ለስራዉ አስፈላጊ በሚሆነው መሬት፤ድንጋይና መሰል የተፈጥሮ ሀብቶች በነጻ ለመጠቀም ወይም ለመገልገል፤ሆኖም በሚጠቀምበት መሬት ላይ ለሚገኙ ስራዎች፤ሰብሎችና አዝርዕት ተገቢዉን ካሳ ይከፍላል፣

- አይሮፕላን በሚያርፍበትና በሚነሳበት መስመሮችና አከባቢዎች ለበረራ አደገኛ የሆኑትን ነገሮች የመከልከል፣ የማንሳት፣የማስነሳት ወይም አስፈላጊው ምልክት እንዲደረግ የማስገደድ፣
- የአይሮፕላን ማረፊያዎችንና አየር ትራንስፖርት ነክ ተግባሮችን እያጠና ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፣በሚፈቀደው ፕሮግራም መሰረት የአይሮፕላን ማረፊያዎችን የመስራት፣የማሻሻልና የመጠገን፣የተሰሩትንም ማረፊያዎች እየጠበቀና እየተቆጣጠረ የማሰተዳደር፣በኢትዮጵያና በውጭ አገርም የናቪጌሽን እርዳታና የአየር ትራፊክ ቁጥጥር አገልግሎት የማበርከት፣
- ደህንነቱን የጠበቀ፣ብቁና የተሟላ የአየር ማመላለሻ አገልግሎት ለህዝብ ማድረሱን የማረጋገጥ፣
- የአየር ትራንስፖርት ጸጥታ ጥበቃ ፕሮግራሞችና ስነ ስርዓቶችን የማስተባበር፣
- ማናኛዉንም የሲቪል አይሮፕላን በጠፋ ወይም በበረራ ላይ እንዳለ አደጋ በደረሰበት ጊዜ የፍለጋና የአስቸኳይ እርዳታ ተግባሮችን ማካሄድና የማስተባበር፣የአይሮፕላን አደጋን የመመርመር፣የአደጋ ምርመራ ሪፖርት አዘጋጅቶ የማውጣት፣
- ባለስልጣኑ በአይሮፕላን ማረፊያ ክልል ውስጥና እንዲሁም ለበረራ ተግባር ለሚያበረክተዉ ማናቸዉም አገልግሎቶችና ድርጅቶች ተገቢውን የዋጋ፣የኪራይ ወይም የሌላ ክፍያ የማስከፈል፣
- ውል ለመግባት፣ለመክሰስና ለመከሰስ፣እንዲሁም ክርክሮችን ለግልግል የማቅረብ፣
- ለስራዉ እንደሚያስፈልገዉ ማንኛዉንም ዓይነት ንብረት የመግዛት፣ የመሸጥ፣ ባለቤት የመሆን፣ የመከራየት ወይም የማከራየት፣
- የአየር ትራንስፖርት ክፍልን በሚመለከት ጉዳይ በኢንተርናሽናል ደረጃ ተወስነው መንግስት ያጸደቃቸውን ውሎች፣እንዲሁም ደግሞ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡትን ደንቦች የማስከበርና የማስፈጸም፡፡

የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት

ድርጅታዊ መዋቅር

9. የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ስር በቦርድ የሚመራ ሆኖ አንድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያለው ሲሆን በስሩ የኦዲትና የአሰራር ጥራት ክትትል አገልግሎት፣የሕዝብ ግኙኝነትና ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ፣የለውጥ ሥራ አመራር ጽ/ቤት፣የሕግ አገልግሎት እና ሁለት ምክትል ሥራ አስፈፃሚዎች አሉት፡፡1^ኛ ምክትል ሥራ አስፈፃሚ የኤርፖርት ስትራቴጂክ ማናጅመንት በስሩ አራት ዳይሬክቶሬቶች ያሉት ሲሆን፣ እነሱም የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ዳይሬክተር፣ የገቢያ ልማት ዳይሬክተር፣ስትራቴጂክ ፕላኒንግና ፋይናንስ ዳይሬክተር እና የሰው ሀብት ልማትና ማኔጅመንት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ 2^{ኛው} ምክትል ዋና ሥር አስፈፃሚ ኤርፖርት ኦፖሬሽን እና መሠረተ ልማት በስሩ ሦስት ዳይሬክቶሬቶችና አንድ አስተዳደር ያሉት ሲሆን፣ እነሱም የኤርፖርት መሠረተ ልማት ዳይሬክተር፣ የኤርፖርት ፋሲሊቲዎች ማኔጅመንትና ጥገና ዳይሬክተር ፣ የግዢ ንብረትና

የጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክተር እና የአዲስ አበባ ቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር ናቸው፡፡

የሰው ኃይል

10. በአጠቃላይ ድርጅቱ 286/(24.6%) ሴቶች እና 875/(75.4%) ወንዶች በድምር 1161 ሠራተኞች ያሉት ሲሆን 981 ቋሚ 180 ጊዜያዊ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ቋሚ ሰራቶኞቹ 10(1.01%) ሁለተኛ ዲግሪ፣ 246/(25%) የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 382(39%) ዲፕሎማና/ሰርቲፊኬት፣ 240(24%) 12ኛ/10ኛ ክፍል፣ 103/(10.5%) ከ10ኛ በታች ናቸው፡፡

የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ

11. ድርጅቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ከመንግስት መደበኛ በጀት፣ቋሚ ዕቃ በጀት፣ እንዲሁም ካፒታል በጀት **/ከራስ ገቢ፣ከመንግስት ግምጃ ቤት፣ከውጭ ብድር ከአገር ውስጥ ባንኮች ብድር/** የሚያገኝ ሲሆን፣ ዝርዝሩ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

ተ/ቁ	በጀት ዓመት	የፀደቀ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	
		ጠቅላላ ድምር	ጠቅላላ ድምር	በጀት በ%
1	2002	501,544,777	544,855,972	109*
2	2003	718,144,667	341,400,108	48
3	2004	1,145,638,390	770,455,679	67
4	2005	1,015,242,429		

*በ2002 በጀት ዓመት በኮምቦልቻ ኤርፖርት ለካሳ ክፍያ በእቅድ ከተያዘው በላይ 51 ሚሊዮን ብር ክፍያ በመፈፀሙ ምክንያት ፐርሰንቱ ከፍ ብሎ መታየት ችሏል፡፡

ድርጅቱ የ2005 ዓ/ም የድርጅቱ ጠቅላላ ስራ ላይ የዋለ በጀት ያልተገለጸው ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ ማስረጃ ያልቀረበለት በመሆኑ ነው፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ለሚገነባቸው መሰረተ ልማቶች ግንባታና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

የኦዲት ትኩረቱ አቅጣጫዎች (Audit Issues)

13. ከላይ የተገለጸውን የኦዲት አላማ ለማሳካት ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና አራት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Sub Issues) የተመረጡ ሲሆን፣ እነርሱም፡-

1. ድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታና ኤሮንቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን በተመለከተ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመወጣት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤
   - 1.1. በድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታና ኤሮንቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን በተመለከተ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችል ተገቢው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤
   - 1.2. ድርጅቱ የሚያስገነባቸው ኤርፖርቶች በጥናት የተደገፉ እና በአነስተኛ ገንዘብና ጊዜ እንዲሁም በተገቢው የጥራት ደረጃ የተገነቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
   - 1.3. ድርጅቱ ለሚያስገነባቸው ኤርፖርቶች የሥራ አፈፃፀም ክትትል ፣ ቁጥጥር ፣ ግምገማና ርክክብ የሚያደርግበት የአሰራር ሥርአት የዘረጋ፣ ተግባራዊ ያደረገና እንዲሁም በታዩት ልዩነቶች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ማረጋገጥ፤
   - 1.4. ድርጅቱ የኤርፖርቶች ኤሮነቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የአከራይና ተከራይ ውል እና መመሪያ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

2. ድርጅቱ የኤርፖርቶች ግንባታና ኤሮነቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ ጋር ተገቢውን ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Crieria)

14. በኦዲቱ ለተመረጡት ሁለት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና፣ አራት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ 29 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት በዋናነት መሰረት የሆኑት የድርጅቱ የመቋቋሚያ አዋጅ፣ደንብ፣ ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የወጣ መመርያ እና የኪራይ ውሎች፣ የመሰረተ ልማት ዳይሬክቶሬት የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፣ የፕሮጅክቶች የግንባታ ውሎች፣ የመ/ቤቱ ዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች፤ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶች ለድርጅቱ ተልከው ስምምነት ላይ ተደርሶባቸዋል፡፡ **በአባሪ 1**ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

የዝርዝር ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

15. ኦዲቱ በዋናነት በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት የተካሄደ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2002 በጀት ዓመት እስከ 2005 በጀት ዓመት ድረስ ባሉት አራት የበጀት አመታት የተሰራውን

ስራ ሲሆን፣ በናሙና በተመረጡ ቦሌ አለማቀፍ ኤርፖርትና ስምንት ኤርፖርቶች / ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጂማ እና ጋምቤላ ኤርፖርቶች /፤ የሥራ ክንውኖችን በአካል በማየት፣ ለስለሺ አማካሪ መሀንዲስ ተወካይ እና ለባለድርሻ አካላት /ለተከራዮች፣ ለኤርፖርት ሴኩሪቲ ሃላፊዎች፣ ለኤርፖርት የፌ/ፖለስ ጥበቃ ሃለፊዎች፣ ለኤርፖርት ሜትሮሎጂ ሃላፊዎች፣ ለኢትዮጵያ ሲቪልአቬዮሽን ባለስልጣን ዳይሬክተር እና ለኢትዮጵያ አየር መንገድ/ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን የማሰባሰብና የማጠናቀር ስራ ተከናውኗል፡፡

16. በመቀጠልም ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና በናሙና ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ለሚመለከታቸው የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ የተገኙ መረጃዎችን የማጠናቀር ሥራ ተከናውኗል ፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

አዋጅ ደንብና መመሪያ በተመለከተ፣

17. ድርጅቱ የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት እንዲያስችለው የመቋቋሚያ አዋጁና ደንቡ እንዲሻሻልለት ያጋጠሙትን ችግሮች በጥናት አስደግፎ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብና ሊያፀድቅ እንዲሁም ድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታ እና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር እንዲያስችለው የወጣውን ደንብ መሰረት በማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣና መመሪያውን ተግባራዊ ሊያደረገ ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

- የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት የተቋቋመበት ዋና አላማ በደንብ ቁጥር 82/95 አንቀጽ 5 ላይ የአየር ማረፊያ ሜዳዎችን የመቆጣጠር ፣የማስተዳደር፣ የመጠገንና አዳዲስ የአውሮፕላን ሜዳዎችን የመገንባት ኃላፊነቶች ለመወጣት በአዋጅ ቁጥር 111/69 ለአየር ትራንስፖርት ባለስልጣን ተሰጥተውት የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በድርጅቱ ማቋቋሚያ ደንብ አንቀጽ 9 እንዳሉ የተሰጡት ቢሆንም የድርጅቱ ዓላማ ሥልጣንና ተግባር ከባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር ጋር የተቀላቀሉና ተሟልተው አለመካተታቸው እንዲሁም የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር በግልፅ አለመታወቃቸው እና በተሻረ ሕግ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ማለትም በቀድሞው የአየር ትራንስፖርት ባለስልጣን መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 111/69 ውስጥ የሚገኙ ለድርጅቱ የተሰጡት መብትና ግዴታዎች የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዮሽን ባለስልጣን እንደገና ለማቋቋም በ1994 ዓ/ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 273/94 የተሻረ መሆኑ ፣ ከድርጅቱ ጋር የሚሰሩ የመንግስት እና የግል ድርጅቶች የግንኙነት ሁኔታ የተገለፀ አለመሆኑ፣ በድርጅቱ መከናወን የሚገባቸው ስራዎች ለባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት መሰጠቱ፣ በደንቡ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላቶች መኖራቸው እና እስካሁን ድረስ ወቅታዊና ማሻሻያ ያልተደረገለት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ ዓለምአቀፍ ሲቪል አቬሽን ድርጅት /ICAO/ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ የግንባታ ደረጃ መመሪያዎች እንደሚጠቀም የተገለጸ ቢሆንም የድርጅቱን ስራ ባህሪ እና በግንባታ ወቅት ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ የግንባታ ማንዋሎች እና ልምዶችን ባገናዘበ ሁኔታ የድርጅቱን ግንባታዎች ለማስተዳደር የሚያስችል መመሪያ እንዳላወጣ ለማወቅ መቻሉ፣
- ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የካቲት 1999 ዓ/ም የወጣ መመሪያ ቢኖርም በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ ክፍተቶች ያሉት መሆኑ ታውቋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ፤-

- በአንቀፅ አምስት በንዑስ አንቀጽ በ5.1 በ5.1.1 ላይ ድርጅቱ ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች እና ትናንሽ መጋዝኖች በስተቀር ሌሎቹን በጨረታ መከራየት እንዳለባቸው የተገለጸ ቢሆንም በንዑስ አንቀጽ 5.3 ደግሞ የማስታወቂያ ቦታዎችን በቀጥታ የመነሻ ዋጋ ማከራየት እንደሚቻል መገለጹ፡፡
- በአንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ በ5.5 ስለ ይዞታዎች ውል ዕድሳት በ5.5.3 ውሉ ታው በሚራዘምበት ወቅት የውሉ አንቀጾች **(እንዲቀየሩ/ እንዲሻሻሉ) ካላስፈለገ በስተቀር)** ቀደም ሲል በተፈረመው ውል ታ ውስጥ የተካተቱ አንቀጾችን ብቻ የያዙ መሆን ይገባቸዋል በሚለው (እንዲቀየሩ/ እንዲሻሻሉ) ካላስፈለገ በስተቀር) የሚለው ሀረግ በድርጅቱና በተከራዮች የተፈረመው እናት ውል ውስጥ የሚገኙ አንቀጾችና ንዑስ አንቀጾች ማለትም የኪራይ ይዞታ መጠን፣ የኪራይ ክፍያ ለመቀነስ ወይም ለመጨመር፣ የውሉ የቆያታ ዘመንን ያለ አግባብ ለመቀያየር በር የሚከፍት መሆኑ፣
- በአከራይና ተከራይ ውል ተከራዮች በብር ወይም ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ካላቸው በውጭ ምንዛሪ መገበያየት እንደሚችሉ የተመለከተ ቢሆንም፣ በመመሪያው ግን ተከራዮች በምን አይነት ምንዛሪ መገበያየት እንዳለባቸው እና በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት ማሟላት የሚገባቸው ነገሮች ያልተካተቱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

19. በ20/03/06 ዓ/ም በቁጥር ሕግ-3/82/06 ከሕግ አገልግሎት ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ከተላከው የድርጅቱ ደንብ እንደገና ለማቋቋም በሂደት ላይ እንደሆነ ከወጣው ረቂቅ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን እንዲሁም ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ የኤርፖርት መሠረተ ልማት ዳይሬክቶሬት የሚያሰራቸውን ግንባታዎች ጥራትና አፈፃፀም ለመከታተል እንዲያመቸው ዓለም አቀፍ ICAO, FAA እና በሀገር ደረጃ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ስታንዳርዶችን እንደሚጠቀም፣ በዚህም መሠረት የማቴሪያል ስታንዳርድን በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስላጣን መስፈርት፣ የአውሮፕላን ሜዳ ጂኦሜትሪን በዓለም አቀፍ ሲቪልአቬሽን ድርጅት መስፈርት /ICAO Standards/ እና ለዲዛይን ግብአት የሚሆኑትን Loadings በFAA Standard በዲዛይን ወቅት በመከተል ተግባራዊ እያደረገ እንደሚገኝ እንዲሁም እነዚህን ባንድላይ ጨምቆ የዲዛይን ማንዋል ለማዘገጀት እየተሰራበት መሆኑ ነገር ግን በግንባታ ወቅት የታዩ ችግሮች የማኑዋል አለመኖር ሳይሆን (በተበታተነም ደረጃ ቢሆን የሚያሰራ ማንዋል ስላለ) በባለድርሻ አካላት መካከል ያለው በአፈፃፀም እና በክትትል ችግር የተከሰቱ መሆናቸውን እንደሚያምኑ በተጨማሪም ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር በ1999 ዓ/ም የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል በሂደት ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

20. ይሁንና ድርጅቱ በወቅቱ ደንቡ እንዲሻሻልለት ያጋጠሙትን ችግሮ በጥናት አስደግፎ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እና በማጸደቅ የድርጅቱ ስልጣንና ተግባር ግልፅ እንዲሆን ባለመድረጉ የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በሚፈለገው ደረጃ ለመወጣት እንዳያስችለው አድርጎታል፡፡እንዲሁም የድርጅቱ የስራ ባህሪ እና በግንባታ ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት ዓለምአቀፍ እና አገርአቀፍ የግንባታ ማንዋሎች እና ልምዶችን ባገናዘበ ሁኔታ የድርጅቱን ግንባታዎች ለማስተዳደር የሚያስችል መመሪያ እንዲወጣ ባለመደረጉ ድርጅቱ በገነባቸው እና እየገነባቸው ባሉ መሰረተ ልምቶች በተያዘላቸው የገንዘብ፣ የጊዜ እና የጥራት ደረጃ እንዳይከናወኑ ትልቅ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ እንዲሁም ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የካቲት 1999 ዓ/ም የወጣው መመሪያ በወቅቱ ያሉትን ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻል ባለመደረጉ በድርጅቱ እና በተከራዮች መሀከል አለመግባበቶች እንዲፈጠር፣ የኪራይ ውሎች እንዲጣሱና እንዳይተገበሩ መንገድ የሚከፈቱ መሆናቸው እና ህጉን የተከተለ የጨረታ ሂደት እንዳይከተል ያደረገው ሲሆን በአጠቃላይ ድርጅቱ ከዘርፉ ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡

ድርጅቱ የተሟላ የሰው ሃይልና አደረጃጀት ያለው መሆኑን በተመለከተ ፣

21. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ የሰው ሃይል ሊኖረው ይገባል፡፡

22. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ መዋቅር የተፈቀደው ቦታና የስው ሀይል ሲታይ ፡-

- በመሰረተ ልማት ዳይሪክቶሬት ስር የሚገኙ የዲዛይን ፕላንና ስታንዳርድ ቡድን እና የኮንተራት አስተዳደር ቁጥጥር ቡድን በመዋቅሩ መሰረት የሚያስፈልጓቸው ባለሞያዎች በቁጥር 30 ሲሆኑ፣ አሁን ስራ ላይ የሚገኙት ባለሞያዎች 14 /46.7%/ ብቻ መሆናቸው እንዲሁም ክልል ኤርፖርቶች በየኤርፖርቶቻቸው የሚከናወኑ ማስፋፊያም ሆነ አዳዲስ ግንባታዎች በጥራት፣ በተያዘላቸው ገንዘብ እና ጊዜ ስለመከናወናቸው ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ለድረጅቱ ዋና መ/ቤት ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል የተቀመጠ ባለሙያ የሌለ መሆኑ ፣
- በክልል ኤርፖርቶች የገበያ ልማት ስራዎችን ሊያከናውን የሚችል ራሱን የቻለ የሰው ኃይል እና አደረጃጀት አለመኖሩ እንዲሁም በዋናው መ/ቤት በገበያ ልማት ዳይሬክቶሬት ባአጠቃላይ ከ12 የስራ መደቦች ውስጥ 7ቱ የስራ መደቦች ብቻ መሟላታቸው በተያያዘም የኤርፖርት ማርኬቲንግ ዓለምአቀፍ ባህሪይ ያለው ከመሆኑ አንፃር ሠራተኞቹ በቂ የሆነ ሥልጠናና ልምድ የሌላቸው መሆኑን ህዳር 30/06 ዓ/ም ከገበያ ልማት ዳይሪክቶሬት ከተፃፈ ማስረጃ ለመገንዘብ ተችለዋል፡፡

23. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ ድርጅቱ መሰረተ ልማቶች ለመገንባት ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር በተለያየ ጊዜ ባለሙያዎችን ለመቅጠር ማስታወቂያ ቢያወጣም (በተለይ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች) ካለው የዘርፉ የዋጋ አንጻር

ማግኘት አለመቻላቸውን ሆኖም ክልል ኤርፖርቶች በየኤርፖርቶቻቸው የሚከናወኑ ማስፋፊያም ሆነ አዳዲስ ግንባታዎች በጥራት፣ በተያዘላቸው ገንዘብ እና ጊዜ ስለመከናወናቸው ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና በድርጅቱ ዋና መ.ቤት ለሚገኘው አካል ሪፖርት ለማድረግ አቅሙ ስለሌላቸው በዋናው መስሪያቤት በኩል እየተፈጸመ እንደሚገኝ፡፡ እንዲሁም በክልል የሚገኙ ይዞታዎች የንግድ እንቅስቃሴአቸው የይዞታዎች መጠን አነስተኛ በመሆኑ ያለው አደረጃጀት ይህንን ለማስተናገድ በሚል ታሳቢ የተሰወደ ሲሆን የገበያ ልማት ዳሬክቶሬት ከኤርፖርቶቹ አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዬችን እንዲያግዛቸው መደረጉ። ሆኖም በነዚህና በአጠቃላይ በአሠራሩ ላይ የሚከሰቱ ክፍተቶች ለማስተካከል የካሊብሬሽን ጥናት እየተካሄደ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

24. ይሁንና ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ የሰው ሃይል እንዲሟላና አደረጃጀት እንዲኖር ባለማድረጉ በዘርፎቹ የሚከናወኑ ተግባራት ላይ የቁጥጥር እና የክትትል ሂደቱ ጠንካራ እና አስተማማኝ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

ኤርፖርቶች ለመገንባት በቅድሚያ የሚደረግ የአዋጪነት ጥናት ስለመኖሩ በተመለከተ፣

25. በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች በአዋጪነት ጥናት ላይ እንዲመሰረቱ እና በጥናቱ መሰረት አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ እና የመልካአ ምድራዊ አቀማመጥ ወዘተ መሰረት ያደረገ የአዋጭነት ጥናት ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብልን አልቻለም፡፡

27. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ ምንም እንኳን የ'ኤርፖርት ይሰራልን' ጥያቄው ከተለያየ አቅጣጫ ማለትም ከህዝብ፣ ከባለ ድርሻ አካላት እንዲሁም ከመንግስት የሚነሳ ቢሆንም፣ የመገንባት ሥራው የሚከናወነው ግን በድርጅቱ የበላይ ቦርድ ከዚህም አልፎ በትራንስፖርት ሚኒስቴር ደረጃ የፕሮጀክቱ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ እና ፖለቲካው አዋጭነት ተቀባይነት ካገኘ በኋላ እንደሆነ፣ ስለዚህ ምንም እንኳን ለሁሉም ኤርፖርቶች ያለቀለት ያዋጭነት ጥናት ማግኘት ባይቻልም በቦርድ እና ከዚያም አልፎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ደረጃ እንዲሰሩ የታመነበትን ምክንያት ማግኘት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ እና የመልካአ ምድራዊ አቀማመጥ ወዘተ በተመለከተ የተሰራ ጥናት ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

29. ስለሆነም በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የሚገነቡ ኤርፖርቶች ግናባታቸው ከመጀመሩ በፊት የአዋጪነት ጥናት የማይደረግላቸው ከሆነ ኤርፖርቶቹ ግንባታቸውን እንዲጀመር ወይም እንዳይጀመር ውሳኔ ለመስጠት ካለማስቻሉም በላይ ብዙ መውአለ ንዋይ ከፈሰሰባቸው በኋላ

የሚጠበቅባቸው አገልግሎት/ጥቅም በወቅቱ ማስገኘታቸውን ወይም አለማስገኘታቸው ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

አብዛኞቹ የድርጅቱ ኤርፖርቶች ፣የይዞታ ካርታ፣ የመሬት አጠቃቀም ካርታ እና መሪ ዕቅድ /Master Plan/ የሌላቸው መሆኑን በተመለከተ፣

30. ድርጅቱ የሚያስተዳድራቸው ኤርፖርቶች መሪ ዕቅድ/Master Plan/ ሊኖራቸው እና በክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ የተገነቡም ሆነ የሚገነቡ የማስፋፍያ እና አዳዲስ ግንባታዎች የኤርፖርቱን መሪ ዕቅድ /Master Plan/ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

31. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው፡-

- አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ፣ ድሬዳዋ፣ መቀሌ አሉላ አባነጋ ፣ ጎንደር አፄ ቴዎድሮስ፣ ጎዴ፣ አሶሳ፣ ኮምበልቻ፣ ሮቤ፣ እና ሰመራ ኤርፖርቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /Title Deed/ ያላቸው ቢሆኑም ባህርዳር ግንቦት 20፣ አክሱም አፄ ዮሀንስ፣ አርባ ምንጭ፣ ጋምቤላ፣ ጅግጅጋ፣ ሁመራ፣ ፓዌ፣ ሽሬ ሜ/ጀኔራል ሀየሎም አርአያ እና ቀብሪደሃር ኤርፖርቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ላሊበላ፣ መቀሌ፣ ጎንደር፣ አክሱምና አርባ ምንጭ እስከ 2015 እ.ኤ.አ ድረስ ማስተር ፕላን /Master Plan/ እና የመሬት አጠቃቀም ፕላን /Land use plan/ እንደተዘጋጀላቸው፣ የአዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት የመሬት አጠቃቀም ፕላን /Land use plan/ እየተሰራለት መሆኑን፣
- ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት ከ10 አመት በፊት መሪ ዕቅድ /Master Plan/ የነበረው ቢሆንም፣ ኤርፖርቱ አሁን ካለው ዕድገት ጋር አብሮ ስለማይሄድ የነበረውን በመከለስ የማሳደግ ዕቅድ /Development Plan/ ለመስራት ስምምነት ላይ መደረሱን፣ እንዲሁም ሌሎች ኤርፖርቶች አሁን ባይኖራቸውም በሂደት እንዲኖራቸው እንደሚደረጉ፣ ነገር ግን ከአሁን በፊት በድርጅቱ የተከናወኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች መሪ ዕቅድ/Master Plan/ መሰረት ያደረጉ አለመሆናቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

32. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ኤርፖርቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /Title deed/ ያላቸው ቢሆንም አንዳንድ ኤርፖርቶች ያሉበት አካባቢ ከከተማ ክልል ውጭ በመሆኑ የሚመለከተው ክልሉን ነው በሚል በተፈጠረ ክፍተት ጊዜ የወሰዱ እንደሆነ፣ እንዳንዶቹ ደግሞ የኤርፖርቱን መገንባት ከመፈለግ አንፃር ቦታውን ነፃ አርገው ካስረከቡን በኋላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ጊዜ የወሰዱ መሆናቸውን። ነገርግን ባሁኑ ሰአት በቀሩት ኤርፖርቶች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖር በቅንጅት እየተሰራበት እንደሚገኝ፡፡ እንዲሁም በክልል ለሚገነቡ ኤርፖርቶች መሪ ዕቅድና የማሳደግ ዕቅድን በተመለከተ ግን ከኤርፖርት ማስፋፊያ ጋር አብሮ የተያያዘ ስለሆነ በሂደት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

33. ሆኖም የድርጅቱ ኤርፖርቶች ፣የይዞታ ካርታ፣የመሬት አጠቃቀም ካርታ እና መሪ ዕቅድ /Master Plan/ የኤርፖርቶችን ይዞታ ለማስከበር፣ በአግባቡ ለመጠቀም፣ ለመገንባት፣ እና

በአግባቡ ለማስተዳደር ስለሚረዱ ሁሉም የድርጅቱ ኤርፖርቶች እንዲኖራቸው አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የድርጅቱ ግንባታዎች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ እና የኮንትራክት ዋጋ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ

34. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ እና ገንዘብ ተገንብተው ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ / **በቀናት/** እና ገንዘብ /**በብር/** ተገንብተው ስለመጠናቀቃቸው ሲታይ፡-

- የጅማ ኤርፖርት የበረራ ሜዳ በ288 /32%/፣ የጂማ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንፃ በ681 /95%/፣ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አሮጌው የመንገደኞች ማስተኛገጃ ህንፃ እድሳት በ207 /38%/፣ የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ በ693 /91%/፣ በቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት የፖሊሶች መኖሪያ ቤት ህንፃ በ65 /15%/፣ የመቀሌ ማቀዝቀዣ መጋዘን በ246 /114%/፣ የባህርዳር ማቀዝቀዣ መጋዘን በ334 /99%/፣ የባህርዳር የቀዝቃዛ መጋዘን ድጋፍ ሰጪ ቢሮ በ559 /266%/ እና የጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንፃ በ1010 /187%/ የመጀመሪያ ርክክብ እስከተደረገላቸው ቀን ከተያዘላቸው የግንባታ ጊዜ መዘግየታቸው እንደዚሁም የመቀሌ የቀዝቃዛ መጋዘን ድጋፍ ሰጪ ቢሮ በ903 /334%/ እና የባህርዳር የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ በ800 /89%/ መዘግየታቸውና ግንባታቸውም ኦዲቱ እስተጠናቀቀበት ታህሳስ ወር 2006 ዓ/ም አለመጠናቀቁ ከድርጅቱ ከተገኙ ማረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በተመሳሳይ ሁኔታ ለነዚህ ግንባታዎች የተያዘላቸው የኮንትራት ዋጋ ሥራ ላይ የዋለው በኦዲቱ ሲታይ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አሮጌው የመንገደኞች ማስተኛገጃ ህንፃ እድሳት በብር 5,305,199.95 /17%/፣ የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ በብር 17,936,899.42 /34%/፣ በቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት የፖሊሶች መኖሪያ ቤት ህንፃ በብር 2,813,452.39 /24%/ ፣ የባህርዳር ማቀዝቀዣ መጋዘን በድርጅቱ አቅም/ሀይል/ የተሰራው ሳይጨምር ለውጭ ኮንትራክተር የተሰጠው ስራ በብር 3,151,187.27 /15%/፣ የባህርዳር የቀዝቃዛ መጋዘን ድጋፍ ሰጪ ቢሮ በብር 1,454,264.54 /20.59%/ እና የጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንፃ በብር 3,863,849.87 /24%/ ግንባታዎቹ የመጀመሪያ ርክክብ እስከተደረገላቸው ቀን ከተያዘላቸው በጀት በድምሩ ብር 34,524,853.44 በለይ ወጪ የተደረገላቸው መሆኑ ከድርጅቱ ከተገኙ መረጃዎቸወ ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ ሲመልሱ፡-

- በዋናነት የበጀት ጭማሪ የሚያሳይብት ምክንያት በዲዛይን ችግር ሲሆን የዋናው መስሪያቤት ህንጻ በተመለከተ የተጠቀሰው ተጫማሪ ወጪ የዋጋ ንረት ማካካሻን /Price Escallation/ ያካተተ እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ እንደሚገባ ገልጸዋል፣

- በተጨማሪም ጊዜያዊ ርክክብ ላልተደረገላቸው ፕሮጀክቶች፡- ጅማ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ፣ የመቀሌ ቀዝቃዛ መጋዘን ድጋፍ ሰጪ ቢሮ፣ የባህርዳር የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ unjustified delays ስለማይታወቁ በኮንትራት ዶክመንት የተገለጸን የማጠናቀቂያ ጊዜን ብቻ በመቀቀስ ይህን ያህል ቀን ዘግይተዋል ማለት እንደማይቻል፡፡ ጊዜያዊ ርክክብ ለተደረገላቸው ፕሮጀክቶች ግን የዘገዩበትን ሊያመላክት የሚችል ማስረጃዎችን ማያያዛቸው ገልጸዋል፣
- የዲዛይን ጥራት ማነስ፣ የስራ ዝርዝር ዝግጅት የተሟላ አለመሆን፣ የተዘጋጀውን ዲዛንና የሥራ ዝርዝር በሚገባ ሳይገመገም /Design Reviewe/ ወደ ግንባታ መግባት፣ ፕሮጀክቶች ከፕላኒንግ እስከ ጨረታ ድረስ በሚገባ ጊዜ ተወስዶ የሥራ ዝግጅት አለማድረግ፣ የሥራ ተቋራጮች አቅም ውስንነት ምክንያት በወጣው መርሃ ግብር መሠረት አለመሥራት፣ የባለሞያዎች /Skilled manpower/ ክህሎት ማነስ፣ በአብዛኛው ዝቅተኛ ዋጋን መሰረት ያደረገ መረጣ ስለሚደረግ ሥራ ተቋራጮች መስፈርቱን አሟልተው ቢገኙም አፈፃፀም ላይ በርካታ ችግሮች መታየት፣ የሱፐርቪዥን /የቁጥጥር/ ክትትል ማነስ እና ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ፣ እንደሀገርም እራሱን የቻለ የቁጥጥር ስታንዳርድ አለመኖር፣ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ መለዋወጥ መኖር እና ይህንን በትክክል ያገናዘበ የዋጋ ንረት ማካካሻ በውለታ ውስጥ አለመኖር፣ የባለሞያዎች እጥረት ለሴክተሩ በአጠቃላይ ጫና መፍጠሩ እና እንደ አሰሪ መስሪያቤት የተጠናከረ የሰውሀይል ባለመኖሩ የቁጥጥርና የኮንትራት አስተዳደሩ መላላት በድርጅቱ የተከናወኑና በመከናወን ላይ የሚገኙ ግንባታዎች ከተያዘላቸው ጊዜ እና ገንዘብ በላይ እንዲወስዱ ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ በ27/03/06 ዓ/ም በቁጥር AID 1/10 /280/06 ከኤርፖርት መሠረተ ልማት ዳይሬክቶሬት ከተገኘው ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፣
- ድርጅቱ በረቂቅ ሪፖርቱ በሰጠው መልስ የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ ግንባታ በዲዛይን ለተከሰተው የግንባታ 33.65% ተጨማሪ ወጪ ግንባታውን ለማጠናቀቅ ሲባል በውለታ ከተያዘለት በላይ መጀመሪያ ማናጅመንቱ 25% ቀጥሎ ወደ 36% ከፍ እንዲል የሥራ አመራር ቦርዱ እንደፈቀደ፣ ነገር ግን ቦርዱ በግንባታ ዋጋ ላይ የተጠቀሰው ጭማሪ ለማጽደቅ የሚያስችል የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ የሚያስረዳ ህገር አቀፍ መመሪያ ስለመኖሩ በማስረጃ ተደግፎ አልቀረበም፡፡
- በተጨማሪም የባህርዳር ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ግንባታ ከተያዘለት የግንባታ ጊዜ በላይ ሊዘገይ የቻለበት ምክኒያት የህንፃው ካኖፒ ትረስ አጥሯል ተብሎ ተገንብቶ ካለቀ በኋላ እንዲፈርስ ተደርጎ ሌላ ዲዛይን ተሰርቶለት እንዲገነባ መደረጉ፣ የቬንቲሌሽን መካኒካል ስራ እንደ አዲስ ዲዛይን ተደርጎ እንዲሰራ መወሰኑ፣ የአሉሙኔም ስራው የግንባታውን 30% የያዘ ሲሆን ጥራቱን ጠብቆ ባለመሰራቱ እና ከሳትኮን ኮንትራክት ተቀብሎ እየሰራ የሚገኝ ንዑስ ኮንትራክትር ስራውን ለመስራት አቅም የሌለው በመሆኑ፣ የአሉሙኒየም እጀታዎች /Alummuniame Handling / እና የተገጠሙ መስተዋቶች ጥራት ስለሌላቸው ከቦታቸው እየተንሸራተቱ የሚገኙ መሆናቸው እና ባህርዳር ላይ ህዳር 29/2005 ዓ/ም ለብሄር ብሄረሰቦች ባአል አድርሱ በመባሉ ችግሮቹ እንደተፈጠሩና ተጨማሪ ጊዜ ሊወስድ እንደቻለ የስለሺ

የግንባታ አማካሪ ድርጅት ተወካይ የኤርፖርቱ ስራ አስኪያጅ ባሉበት በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

37. ከላይ እንደተመለከተው አብዛኛው በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ እና ገንዘብ ተገንብተው ባለመጠናቀቃቸው በሚፈለገው ጊዜ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ አገልግሎት ካለመመስጠታቸውም በተጨማሪ በመዘግየታቸው በየጊዜው ለተከሰተው የዕቃዎች የዋጋ መናር እንዲጋለጡና በተለይ በጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንጻ ግንባታ የሚወጣው ወጪ በጣም ከፍተኛ እንዳይሆን ታስቦ ግንባታው የጥራት ደረጃው ዝቅ እንዲል ተደርገዋል፡፡

የተጠናቀቁ ግንባታዎች ርክክብ እና በተገባላቸው ውል መሠረት ስለመሰራታቸውና በታዩ ግድፈቶች ላይ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፣

38. ግንባታቸው የተጠናቀቁ መሰረተ ልማቶች ጊዜያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኋላ የመጨረሻ ርክክብ ሊደረግና በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ድርጅቱ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- የተጠናቀቁ ግንባታዎች የርክክብ አፈጻጸም ሲታይ የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ሕንፃ ፣ የባህርዳር ቀዝቃዛ መጋዘን፣ የጋምቤ የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንፃ እና የጅማ የአውሮፕላን ማኮብኮቢያ ሜዳ ግንባታ በቅደም ተከተል እ.ኤ.አ በህዳር 7/2009 ፣ በህምሌ 29/2011 ፣ በሰኔ 06/2011 እና በሚያዚያ 27/2012 ግንባታቸው ተጠናቆ ጊዜያዊ ርክክብ የተደረገላቸው ቢሆኑም ያላቸውን የግንባታ ግድፈት በመለየት የመጨረሻ ርክክብ መደረግ ከነበረበት ቀን እንደ ቅደም ተከተላቸው በ388 ፣ በ480 ፣ በ174 እና በ90 ቀናት መዘግየታቸው ታውቋል፣
- እንደዚሁም የአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል ግንባታ ጊዜያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኋላ የመጨረሻ ርክክብ በማድረግ በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶችን /Defects/ በመለየት ድርጅቱ ህጋዊ እርምጃ በወቅቱ ሊወስድ አለመቻሉ፣
- የህንፃው ጣሪያ በክረምት ወቅት ዝናብ የሚያንጠባጥብ በመሆኑ መንገደኞች፣ ሰራተኞች፣ ተከራይተው በንግድ ተሰማርተው የሚገኙ ነጋዴዎች ለ10 አመታት ያህል በፍሳሽ ከመቸገራቸውም በተጨማሪ አብዛኛው የኤርፖርቱ ተጠቃሚዎች የውጭ ዜጎች በመሆናቸው በአገር ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳደሩ፣
- ድርጅቱ ህንፃውን የመጨረሻ ርክክብ ሳያደርግ ለ10 አመታት ያህል በመጠቀሙ፣ በግንባታ ወቅት የታዩ ግድፈቶችን በወቅቱ እንዲስተካከሉ ማስደረግ ያልቻለ በመሆኑ፣ በግንባታ ወቅት አማካሪ ድርጅት የነበረው በተለያየ ጊዜ የድርጅቱን ስም በመቀያየሩ ለማግኘት አለመቻሉ እና የስራ ተቋራጩ ብዙ ወጪ በማውጣት ጥገና ቢያደርግም መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ ባለመቻሉ ምክንያት ድርጅቱ የታዩት ግድፈቶችን መሰረት

በማድረግ ጉዳዩን ወደ ህግ ቢወስደው ሊያሸንፍ የሚችልበት እድል የጠበበ በመሆኑ ከተቋራጩ ጋር መደራደርን በመመምረጡ የህንፃውን ጣሪያ ሙሉ ለሙሉ ለመቀየር በግርድፉ ከሚየስፈልገው USD 3,210,570.00 ውስጥ 60% 1,926,342 USD እንዲሸፍን የተገደደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግልጫ ላይ ሲመልሱ ቋሚ ርክክብ ከታሰበው የጊዜ ገደብ ከአመት በላይ መቆየቱ ከማንም በላይ ተጎጅ የሚያደርገው የሥራ ተቋራጩን እንደሆነ፡፡ምክንያቱም ለችግሮች ተጠያቂነትን ጊዜ/defect liability period/ በውለታው ከተጠቀሰው የአንድ አመት ጊዜ በላይ ሰለሚያራዝም መሆኑ፡፡ቋሚ ርክክብ ለማድረግ ረዘም ያለ ጊዜን ለሚወስዱ ሥራ ተቋራጮች ውለታ ማቋረጥ/termination/ የማይመርጡት ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚወስድና አላስፈላጊ ወጪ የሚያስወጣ መሆኑን፡፡ለዚህም ሲባል በኮንትራክት ውስጥ ብዙ ግዜ ችግሮችን በመግባባት ለመፍታት/amicable settlement/ ቅድሚያ እንደሚሰጡት፡፡ በተቻለ መጠን ሥራ ተቋራጮች ለዘገዩበት ጊዜ ያህል የሚያገለግል ዋስትና ማቅረብ እስከቻሉ ድረስና በተጨማሪም የታየው ችግር የኤርፖርቱን የሥራ ክንውን እስካላጓተተ ድረስ ቋሚ ርክክብ ለማድረግ ጊዜ መፍጀቱ እንደ ዋና ችግር እንደማይቆጥሩት ገልጸዋል፡፡

41. ይሁንና ግንባታዎች በተያዘላቸው የዋስትና ቀናት ግድፈቶቻቸው ተለይተውና ተሰተካክለው የመጨረሻ ርክክብ የማይደረግላቸው ከሆነ፣ ድርጅቱ ላላስፈላጊ ወጪ እና ኪሳራ ሊዳርጉት ከመቻላቸውም በተጨማሪ ህንፃዎቹ የተጠቃሚውን ፍላጎት በወቅቱ እንዳያሟሉና የግንባታወቹ ጉድለቶች በድርጅቱም ሆነ በሀገር ገጽታ ላይ ተጽእኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

ኤርፖርቶች አስተማማኝ ደህንነት ያላቸውና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን በተመለከተ

42. ድርጅቱ ለአይሮፕላኖች፣ ለመንገደኞችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝና ቀልጣፋ የኤርፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ኤርፖርቶች የዙሪያ አጥር፣ የሌሊት የጥበቃ መብራቶች፣ የጥበቃ ማማዎች፣ የግኑኝነት መሳሪያዎች፣ የአቬዮሽን ሜትዎሮሊጂ አገልግሎቶች፣ የእሳት አደጋ መከላከያና ማጥፊያ እና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የሌላቸው ወይም ያልተሟላና አስተማማኝ ያልሆኑ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታቸው እንደሚከተለው ታይቷል፡-

የኤርፖርቶች ዙሪያ አጥር እና የሌሊት የጥበቃ መብራቶች የተሟሉና አሰተማመኝ አለመሆናቸው በተመለከተ፡-

በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ኤርፖርቶች፣

- በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኘው የኮምበልቻ፣መቀሌ፣አክሱም፣ጎንደር፣ እና ጅማ ኤርፖርቶች ዙሪያ አጥር ያላቸው ቢሆኑም አጥሮቻቸው ያልተሟሉና ሰውና የተለያዩ እንስሳቶች የሚያስገቡ ክፍተት ያሉባቸው መሆኑ፣

- ባህርዳር ኤርፖርት ዙሪያ አጥር ክፍተት ያለው ከመሆኑም በላይ በጥቅጥቅ ደን የተሸፈነና የተለያዩ አደገኛ የዱር እንስሳት ያሉበት በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ስለ ኤርፖርቱ ዙሪያ አጥር ሁኔታ የማይታወቅ መሆኑ እንዲሁም የጋምቤላ ኤርፖርት ባለው ጥቅጥቅ ደን ምክንያት የተሟላ ዙሪያ አጥር ይኑረው አይኑረው የማይታወቅ መሆኑ፣
- አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት ዙሪያ የተተከሉ የጥበቃ መብራቶች /ፓውዛዎች/ ብር 9 ሚሊዮን ወጪ የተደረገባቸው ቢሆኑም መስጠት የሚገባቸውን ጥቅም /አገልግሎት/ በሚፈለገው መልኩ ሳይሰጡ በተደጋጋሚ ጊዜ የሚጠፉበትና የሚበላሹበት ሁኔታ መኖሩንና ለዚህ እንደምክንያት የሚቀርበው የኤሌክትሪክ ገመዶች መቅለጥ መሆኑን፣ ይህም በኤርፖርቱ ዙርያ መብራቶች ቢኖሩም፣ በግዢ ችግር ምክንያት ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን የኤርፖርቶች ጥበቃ መምሪያ ሃላፊ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ የገለጹ መሆኑን፣
- እንዲሁም የመቀሌ፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጋምቤላ እና ጅማ ኤርፖርቶች የጥበቃ መብራቶች /ፓውዛዎች/ የሌላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

- አሁን ስራ ላይ የሚገኘው የጂማ የውሮፕላን የበረራ ሜዳ ገበያተኞች አቋርጠው ሲያልፍ /ነሐሴ 2005 ዓ/ም/
- የጎንደር አፄ ተዎድሮስ ኤርፖርት ክልል በመጣስ በአውሮፕላን ማኮብኮቢያና ማረፍያ ሜዳ ላይ ከሚገኙ አውሮፕላኑ/ በትክክለኛ ቦታው እንዲያርፍ ከሚረዱ ማንነታቸው ባልታወቁ አካላት ከተሰበሩ ከአስራ አምስት መብራቶች አንዱ፡፡ /ጥቅምት 2006 ዓ/ም/

በየኤርፖርቶቹ ደረጃቸውን የጠበቁ ፣ በቂ እና አስተማማኝ የጥበቃ ማማዎችና የግንኙነት መሳሪያዎች ስላለመኖራቸው

- በናሙና በታዩ መቀሌ፣ አክሱም፣ ጎንደር፣ ባህርዳር ፣ ጋምቤላ እና ጅማ ኤርፖርቶች ያሉ የጥበቃ ማማዎች ከወዳደቁ ቆርቆሮዎች የተሰሩና ጥንካሬ የሌላቸው መሆኑ፣ ዝናብ እና ፀሐይ በአግባቡ የሚከላከሉ አለመሆናቸው፣ የተወሰኑት መሬት ላይ በመሰራታቸው በኤርፖርቱ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለማየት የማያስችሉ መሆናቸው፣ ከአንድ የጥበቃ ማማ ወደ ሚቀጥለው የጥበቃ

ማማ ያለው ርቀት ሰፊ በመሆኑ በመሀከል የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማየትና ተገቢ ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚያስቸግር ከመሆኑም በተጨማሪ በጥበቃ የተሰማሩ አባላት ማንኛውም ችግር ቢያጋጥማቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል ምንም አይነት የመገናኛ መሳሪያ የሌላቸው መሆኑ፡፡

- በአክሱም ኤርፖርት ከጥበቃ ማማዎች አንዱ መስከረም 2006 ዓ/ም
- በአክሱም ኤርፖርት በመከላከያ ከተገነቡ ደረጃቸው ከጠበቁ የጥበቃ ማማዎች አንዱ መስከረም 2006 ዓ/ም

በኤርፖርቶች ውስጥ የሚገኙ የፍተሻ ማሽኖች በአግባቡ አገልግሎት የሚሰጡና አስተማማኝ ስላለመሆናቸው

- በናሙና በታዩ አዲስ አበባ ቦሌ፣ መቀሌ፣ አክሱም፣ ጎንደር፣ ጋምቤላ እና ባህርዳር፣ ኤርፖርቶች የፍተሻ ማሽን ቢኖሯቸውም፤ በተደጋጋሚ ጊዜ የሚበላሹ እና በአግባቡ አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው መታወቁና የችግሩ ጥልቀት በዝርዝር ሲታይ ለምሳሌ፤ በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት በመግቢያ በሮች መካከለኛ መጠን ያላቸው የራፒስካን ስሪት ኮንቬንሽናል ኤክስሬዮች የእጅና የጭነት ሻንጣዎች የፍተሻ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ማሽኖች ከተገዙና አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ ስድስት አመት ብቻ የሆናቸው ቢሆኑም ከፍተኛ የአሰራር ብቃት ማነስ፣የምስል መቆራረጥ እንደሚታይባቸውና በተደጋጋሚ ጊዜ ብልሽት እንደሚያጋጥማቸው ይህ ሁኔታ የሴኩሪቲ አፈፃፀም አስተማማኝነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳረፉም በተጨማሪ የሴኩሪቲ ሰራተኞችና የድርጅቱ የቴክኒክ ባለሞያዎች በመሳሪያዎቹ ላይ ያላቸውን መተማመን በእጅጉ ዝቅተኛ ማድረጉ እና ስጋት መፍጠሩ መታወቁ ፣
- በቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት በተርሚናል ሁለት የጭነት ሻንጣዎችን ለመፈተሽ አጠራጣሪ ፈንጂ የሚመስሉ ቁሳቁሶች የሚለዩ እንዲሁም ፈንጅ እንዲለዩ ተደርገው የተሰሩ ሁለት መፈተሻ መሳሪያዎች /Explosive Detection System/ የተተከሉት ከአስር አመት በፊት ከኤርፖርቱ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሲሆኑ፣ በነበራቸው የብቃት ማነስና የሴኩሪቲ ፍላጎትን አለሟሟላት እስከ

1999 ዓ/ም አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ መሆናቸው፣ በ1999ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ ከመሳሪዎቹ አቅራቢ ድርጅት ጋር በመነጋገር በመሳሪያዎቹ Detection Software ማሻሻያ ተደርጎላቸው በአመት ከብር 3 ሚልዮን በላይ ዋጋ ያለው የጥገና የመለዋወጫ አቅርቦት ስምምነት ተደርጎ ለመሳሪያዎቹ በየወቅቱ ሰርቪስና እድሳት እየተደረገላቸው አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ቢሆንም፣ EDS የመሳሪያዎቹን አፈፃፀም ደረጃ በማሳደግ የኤርፖርቱ የሴኩሪቲ የአፈጻፀም ደረጃን ለማሻሻል እና ለጥገና አገልግሎትና ለመለዋወጫ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ እንደሚያስፈልግ መጋቢት 2005 ዓ.ም የሴኩሪቲ መሳሪያዎች ግዢ አፈፃፀም ሂደት ለመወሰን እንዲረዳ ከተዘጋጀ ሰነድ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- በመቀሌ አሉላ አባ ነጋ ኤርፖርት የሚገኙ ራፒስካን የፍተሻ ማሽኖች በየግዜው የሚበላሹ መሆናቸው፤ ለምሳሌ ከ05/01/02ዓ/ም እስከ 19/12/02ዓ/ም 10/አስር/ ፣ ከ05/01/03ዓ/ም እስከ 01/10/03ዓ/ም 7/ሰባት/፣ ከ04/04/04ዓ/ም እስከ 10/12/04ዓ/ም 7/ሰባት/ እና ከ15/02/05ዓ/ም እስከ 21/05/05ዓ/ም 3/ሦስት/ ጊዜ ብልሽት ያጋጠማቸው ሲሆን እንዲሁም ሂማን የፍተሻ ማሽን ከ19/04/02ዓ/ም እስከ 26/11/02ዓ/ም 4/አራት/፣ ከ04/05/03ዓ/ም እስከ 27/10/03ዓ/ም 3/ሦስት/፣ ከ01/01/04ዓ/ም እስከ 28/12/04ዓ/ም 14/አስራ አራት/ እና ከ04/01/05ዓ/ም እስከ 30/10/05ዓ/ም 9/ዘጠኝ/ ጊዜ ስለመበላሸታቸው ከመቀሌ አሉላ አባነጋ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ኦፕሬሽንና ፋሲሊቲ-- ለመቀሌ ኤርፖርት አስተዳደር በ03/11/05ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር መኤ/ኦፕ/ፋ/131/05 በተገኘ የጽሁፍ ማስረጃ ለመረዳት መቻሉ፣
- እንዲሁም ጅማ እና ሽሬ ኤርፖርቶች የፍተሻ ማሽን የሌላቸውና ፍተሻው የሚከናወነው በሰው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኤርፖርቶች የተሟላ የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልገሎት እያገኙ ስላለመሆናቸው

- የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በጅንካ፣ በአዋሣ፣ በባሌ ሮቤ፣ በኮምቦልቻና በሰመራ መጋቢ አውሮፕላን ማረፊያዎች ሲገነባ፣ መረጃ እንዳልሰጣቸው፣ ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ባገኙት መረጃ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ ለመገንባት እንዲችሉ እንዲሁም የጣቢያ ማቋቋሚያ፣ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለመስጠት ለሚመደቡ ባለሙያዎችና የሥራ መገልገያዎች የሚሆን ምቹ ቦታና ቢሮ እንዲዘጋጅላቸው በቁጥር AMD/ 212 / ሚያዝያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅትን ቢጠይቅም አሁንም ድረስ ምላሽ አለማግኘታቸውን ኤርፖርቶቹ የሚቲዎሮሎጂ የአየር ትንበያ መረጃ አገልግሎት

እያገኙ አለመሆኑን በድርጅቱ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት መቻሉ፣

- የአውሮፕላን በረራ በሚደረግበት ወቅት ተቆጣጣሪው ለአብራሪው መግለፅ ካለበት መካከል ዋነኛው የዕለት የአየር ሁኔታ ቢሆንም፣ በጋምቤላ ኤርፖርት ምንም አይነት የአየር ሁኔታ/ሜትሮሎጂ/ አገልግሎት የሌለ በመሆኑ በስራቸው ላይ ትልቅ ችግር እንደፈጠረባቸው እና ከክልሉ የሜትሮሎጂ ቢሮ ጋር በመነጋገር በኤርፖርቱ ቅጥር ግቢ መሳሪያዎች እንዲተከሉ ቢደረግም የኤርፖርት ሴኩሪቲ ሃላፊ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት በመከልከሉ ኦዲቱ እስተከናወነበት ቀን አገልግሎት ሊሰጥ ያልቻለ መሆኑ እንዲሁም በአውሮፕላን ማረፊያና መነሻ ሜዳ ላይ የንፋስ አቅጣጫ ጠቋሚ ጨርቅ /Wind Sock/ በሚበላሽበት ወይም በሚቀደድበት ወቅት እንዲስተካከል ለኤርፖርቱ ሃላፊ ጥያቄ ቢያቀርቡም፣ ከድርጅቱ ዋና መ/ቤት በቂ ጨርቅ እንዳልተላከላቸው በመግለጽ ጥያቄያቸውን ውድቅ እንደሚያደርግባቸውና የሜትሮሎጂ አገልግሎት ካለመኖሩ በተጨማሪ የንፋስ አቅጣጫን ለይቶ ለሚያርፍና ለሚነሳ አውሮፕላን የመነሻና የማረፍያ ፍቃድ ለመስጠት እንደሚቸገሩ የኢትዮጵያ ሲቪልአቬዮሽን ባለስልጣን የጋምቤላ ኤርፖርት የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪ ሃላፊ ገልጿል፡፡

ኤርፖርቶች የተሟላ የእሳት አደጋ መከላከያና ማጥፊያ እና የውስጥ ለውስጥ መንገድ /Accssess Road / የሌላቸው ስለመሆኑ፡፡

- በናሙና በታዩ መቀሌ፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጅማ እና ጋምቤላ ኤርፖርቶች የኤርፖርቱን ክልል 360 ዲግሪ ሊያሳይ የሚችል የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ ማማ /watch room/ ፣ እሳት አደጋ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት በስራ ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች ምቹ ማረፍያ ቦታና ቢሮ የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም ኤርፖርቶቹ ክልል ውስጥ ማንኛውም አደጋ ሲያጋጥም ወይም አደጋው ከመድረሱ በፊት ለመቆጣጠር የሚያስችል የውስጥ ለውስጥ መንገድ /Accesses Road /የሌላቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

44. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግልጫ ላይ ሲመልሱ እንደ ሀገር እነዚህን የኤርፖርት መሠረተ ልማቶች በአንዴ የሚሟላት አቅሙ እንደሌላቸው ደረጃ በደረጃ ለማሟላት ጥረት እንደሚያደርጉ፡፡ ይሁንና አፋጣኝ ምላሽና አስቸኳይ ውሳኔን ለሚፈልጉ ኤርፖርቶች ግን አስፈላጊውን ምላሽ እየሰጡ እንደሚገኙ፡፡ ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በሰሜን አትዮጵያ ለሚገኙ ኤርፖርቶች እነዚህን የኤርፖርት መሠረተ ልማቶች ለሟሟላት ግንባታ መጀመራቸው፡፡ እንዲሁም ሁሉም ኤርፖርቶች የጥበቃ ማማና አጥር ሲኖሯቸው በህብረተሰቡ የአጠቃቀም ችግር የተነሳ ጉዳት ለደረሰባቸው ተከታታይ የሆነ ጥገና እንደሚደረግላቸው በተጨማሪ የጥበቃ ማማን በተመለከተ ተጨማሪ ሥራዎችን በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑንና ከአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት በስተቀር ሌሎቹ ኤርፖርቶች የሌሊት መብራት እንደሌላቸው፣ ለወደፊት ግን ይህ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ የሚፈጽም መሆኑን ገለጸዋል፡፡

45. ***ሆኖም ኤርፖርቶቹ ደህንነታቸው በአግባቡ ባለመጠበቁ የሚከተሉት ችግሮች ተከስተዋል፡-***

- *የባህርዳር ኤርፖርቶች የኤርፖርቱ ዙሪያ አጥር ብዙ ቦታዎች ላይ ተቆራርጦ ክፍት በመሆኑ ምክንያት፣ አንድ ጊዜ 75 ከብቶች ከሌሊቱ 6 ሰአት፣ሌላ ጊዜ 61 ከብቶች ከሌሊቱ 5 ሰአት ተኩል ላይና በተጨማሪ በግንቦት ወር 2005 ዓ/ም አንድ ጊዜ 34፣ ሌላ ጊዜ 25 ከብቶች በቀን በኤርፖርቱ ክልል ውስጥ መግባታቸውና በሚያርፍና በሚነሳ አውሮፕላን ላይ አደጋ የማድረሳቸው እድል ከፍተኛ መሆኑ፣*
- *ጅማ ኤርፖርቱ የማስፋፍያ ስራ ሲደረግለት፣ በዙሪያ አጥሩ ብዙ ክፍተቶች በመፈጠራቸው ከብቶች፣በጎች፣ቀበሮዎች እና ሌሎች እንስሳዎች የሚውሉበት፣ በተጨማሪ በተለይ በገበያ ቀን በርካታ ሰዎች የበረራ ሜዳውን* /Run way/ *እያቋረጡ ከገጠር ወደ ከተማ፤ከከተማ ወደ ገጠር የሚመላለሱበት መሆኑ፣*
- *በጎንደር አፄ ቴዎድሮስ ኤርፖርት በ*07/02/99*ዓ/ም አንድ፣ በ*11/09/03 *ዓ/ም ሦስት እና በ*21/11/05 *ዓ/ም ሌሊት አስራ አንድ በድምሩ አስራ አምስት የአውሮፕላን ማኮብኮቢያና ማረፍያ ሜዳ ላይ የሚገኙ አውሮፕላኑ በትክክለኛ ቦታው እንዲያርፍ የሚረዱ መብራቶች ማንነታቸው ባልታወቁ አካላት መሰበራቸውና ኦዲቱ እከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ድርጊቱን ማን እንደፈፀመው የማይታወቅ መሆኑ፣*
- *መቀሌ የኤርፖርቱ ዙሪያ አጥር የተለያዩ እንስሳትና ሰው የሚያስገባ ትላልቅ ቀዳዳዎች ያሉበት በመሆኑ በግንቦት* 28/2005 *ዓ/ም ማታ* 1፡15 *ሰዓት በሚያርፈው የኢትዮጵያ አየር መንገድ* Q 400 *የበረራ ቁጥር* 108 *ሰባ ስምንት ሰው እንደጫነ ከጅብ ጋር በመጋጨቱ በሰው ላይ አደጋ ባይደርስም ለሁለት ቀን ያለ ስራ በመቆሙና ሰው ሳይጭን በመመለሱ ከመቀሌ አዲስ አበባ ባለው ሂሳብ ሲሰላ የጥገና ወጪውን ሳይጨምር ብር*1,722,240.00 *አየር መንገዱን ማሳጣቱ ፣*
- *በአጠቃላይ ድርጅቱ የዙሪያ አጥር፣ የሌሊት የጥበቃ መብራት፣ የፍተሻ ማሽን እና ሌሎች የደህንነት ስጋት የሆኑ ችግሮችን በወቅቱ መፍታት ካልቻለ በመንገደኞች እና በአውሮፕላኖች ላይ አደጋ የመከሰቱን እድል ሰፊ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ በህይወትና በንብረት ኪሳራ ሊያደርስ ይችላል፡፡*

የድርጅቱ ግንባታዎች ደረጃቸውን የጠበቁና በውሉ መሰረት እየተገነቡ መሆናቸውን በተመለከተ፡-

46. *በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በግንባታ ኮንትራት ውሉ በተቀመጠው መስፈርት* /Specification/ *መሰረት መግንባታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡*
47. *ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የጋምቤላ፣ የባህርዳር ኤርፖርቶችና የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ግንባታዎች አፈጻጸም ሲታይ፡-*

በጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ የታዩ ችግሮች፡-

- *ወደ ሁለተኛ ፎቅ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ መቀመጫ ክፍል የሚወስደው የብረት ደረጃ መውጫ የእግር መርገጫ ጣውላዎች በአግባቡ በብሎን የታሰሩ አለመሆናቸው፣*

የጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ ወደ ሁለተኛ ፎቅ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ መቀመጫ ክፍል የሚወስደው የብረት ደረጃ መውጫ የእግር መርገጫ ጣውላዎች በአግባቡ በብሎን ያልታሰሩ ስለመሆናቸው የሚያሳይ ፎቶ /ነሐሴ 2005 ዓ/ም/

- በውለታ ሠነዱ የተመለከተውና በዲዛይኑም ላይ የሚታየው የውስጥ ቢሮዎች መክፈያ /Partitions/ ከቀላል ቁስ የሚሠራው ግድግዳ በአንደኛ ፎቅ ላይ የሥራ አስኪያጅ ቢሮ የሚገኝበት ወለል በሙሉ አለመሰራቱ፡፡
- በአጠቃላይ በኤርፖርት የሚገኙ ግንባታዎች ሁሉ የበርና የመስኮት እጀታዎች የተበላሹና የማያገለግሉ ከመሆናቸውም በላይ የሌሉበትም ሥፍራ መኖራቸው፣
- በመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ በፊት ለፊት ከበስተኋላ ላይ የሚገኙት ባለ 860 ሳ./ሜ ስፋት የአልሚኒየም በርና መስኮት /French Windows and Doors / ልኬታቸው ከውለታ ሠነዱና ከዲዛይኑ ጋር የማይጣጣሙና ያነሱ መሆናቸው፣ **በአባሪ 2 ተያይዟል**
- በህንፃው በውለታ ሰነዱ ተራ ቁጥር ዘጠኝ ዜሮ አንድ የተመለከተው ከፊል ብርሃን አስተላላፊ መስታወት "Tinted and Figured Glass" ያልተገጠመ መሆኑ፣
- ከመንገደኞች የጉዞ መጠባበቂያ አጠገብ ያለው የመብራት መቆጣጠሪያ ከዋናው ኃይል መስመር ጋር ንክኪ ያለው እና አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑና በመንገደኞች መግቢያ የኤሌክትሪክ መቀበያ ሶኬት በተገቢው ቦታ ባለመገጠሙ በመንገደኞች መግቢያ መገጠም የነበረበት የደህንነት መፈተሻ ማሽን ያለ ቦታው በመንገደኞች መውጫ በር እንዲገጠም የተደረገ መሆኑ፣

የጋምቤላ መንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ የኤሌክትሪክ ዝርጋታ በአግባቡ ባለመሰራቱ የመብራት መቆጣጠሪያው በኤርፖርቱ የኤሌክትሪክ ባለሞያ ሲሞከር እሳት ያለውና በሠራተኞች እና በመንገደኞች ላይ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል የሚያሳይ ፎቶ ፡፡ /ነሀሴ 2005 ዓ/ም/

- ህንፃው ከአመት በፊት የተጠናቀቀና ርክክብ ተደርጎበት አገልግሎት መስጠት የጀመረ ቢሆንም በውለታ ሰነዱ መሰረት ተጠባባቂ የኃይል ማመንጫ ጀኔሬተር የሌለው መሆኑ፣
- በውለታ ሠነዱ የተጠቀሰው የድምጽ ማጎልበቻ መሣሪያ በህንፃው ውስጥ ያልተገጠመ መሆኑ፣
- የህንፃው የሙቀት መቆጣጠሪያ መሣሪያ በውለታ ሠነዱ መሠረት በህንጻው ያልተገጠመ መሆኑ፣
- የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ በውለታ ሰነዱ መሠረት በህንፃው ያልተገጠመ መሆኑ፣
- በዲዛይኑና በውለታ ሰነዱ የተመለከተው የደንበኞች ዕቃ መውሰጃ ማሽን በመዳረሻም ሆነ ከፍተሻ በኋላ የሌለ መሆኑ፣ የአማካሪው እና የድርጅቱ ይሁንታ ያገኘ የተፈረመበት ናሙና ባለመገኘቱ የውለታ ሰነዱ በሚያዘው መሰረት በዋናው ህንፃ የቧንቧ ገጠማ ሥራው ደረጃውን የጠበቀና መስፈርቱን ያሟላ የሳኒተሪ ፊክሲቸር መገጠማቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ለአካል ጉዳተኞች እና ለካፍቴሪያ አገልግሎት ወደ ካፍቴሪያው 1ኛ ፎቅ የሚወሰደው አሳንሰር ጋሪ በአርክቴክቸራል ፕላኑ መሠረት ያልተገጠመና በቦታው የሌለ መሆኑ፣
- በክብር እንግዶች ክፍል (VIP Room) የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እና በምግብ ማዘጋጃ ኩሽና (Kitchen) ማጠቢያ፣ መደርደሪያ፣ ምድጃ፣ እና የመሳሰሉ የማድ ቤት ቁሳቁሶች ያልተገጠሙ መሆናቸው፣
- በውለታ ሰነዱ የተመለከቱት የአልሙኒየም የደረጃ መከለያ በካፊቴሪያው ሜዛኒን ወለልና በህንፃው በረንዳ አካባቢ ከጎንና ከጎን ግራና ቀኝ አንፀባራቂ ብርማ ቀለም ተቀብቶ በባለ 3.25 ኢንች የቧንቧ ብረት ተለውጦ መሰራቱ ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት የሚያመጣ መሆኑ፣
- በህንፃው የመንገደኞች መቆጣጠሪያ የሚገኙ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ የውስጥ ቢሮዎች ሁሉም በውለታ ሰነዱ መሰረት የመስኮት ክፈፋቸው በአልሙኔየም መሆን ሲገባው ከቀረሮ በተዘጋጀ እንጨት ፍሬማቸው እንዲሰራ መደረጉ፣

በጋምቤላ ኤርፖርት በጥበቃ ቤት ላይ የታዩ ችግሮች

- የውሃ አቅርቦት የሌለው መሆኑ፣
- የሽንት ቤት በርና መስኮት ስለማይከፈት የተበላሸና አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣
- የሃይል አቅርቦት ባለመኖሩ መብራት የሌለው መሆኑ፣
- ከአሉሚኒየም የተሰሩ በርና መስኮቶች በውለታ ሰነዱና ዲዛይኑ ላይ ከተመለከተው መጠን ልኬት አንሰው መገጠማቸው፣
- 07 Glazing Finishing Work, 7-2,7-2-08 ,PVC Tiles Size 30 x30 x 2mm ,Totally Dismanteled (እየተበላሸ መሆኑ፣)

<u>09 Glazing</u>

ተ.ቁ.	ውለታ ሰነዱና ዲዛይኑ ላይ የተመለከተው መጠን	ተገንብቶ የሚገኘው መጠን
	5mm Thick Tinted Glass	Clear Glass

የጋምቤላ ኤርፖርት የጀነሬተርና የውሃ ፓምፕ ቤት ላይ የታዩ ችግሮች

- በግንባታው ውስጥ የጀነሬተር ማሽን፣ የውሃ ፓምፕ በውለታው መሠረት የሌሉ መሆናቸው፣
- የኤሌትሪክ ገመዶች ለአደጋ በተጋለጠ መልኩ ተዝረክርከው የሚታዩ መሆናቸው፣
- በዙሪያው የተቀመጠው የባዞላ ድንጋይ በመፍረስ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣
- ህንፃው በአጠቃላይ አገልግሎት መስጠት አለመጀመሩ፡፡

<u>05 Aluminium Work, Aluminium Window Frame</u>

ተ.ቁ.	ውለታ ሰነዱና ዲዛይኑ ላይ የተመለከተው መጠን	ተገንብቶ የሚገኘው መጠን
	Type W24 Size 135 x 90 ሳሜ	135 x 70 ሳሜ

የጋምቤላ ኤርፖርት የምድረ ግቢ ሥራና የመኪና ማቆሚያ ላይ የታዩ ችግሮች፡-

- የመኪና ማቆሚያ አስፋልት በመፈራረስ ላይ መሆኑ፣
- በውለታ ሰነዱ ከተጠቀሱ 12 /አስራ ሁለት የውጭ/ /የመንገድ/ መብራቶች ውስጥ 6 /ስድስቱ/ ብቻ መሰራታቸው፡፡

48. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ፡-

<u>**በጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ግንባታ የታዩ ችግሮች**</u>

- የብረት መወጣጫ መሰላሉ በአግባቡ የሚሰራና አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ መሆኑ፡፡
- ችግር ያለባቸውን ለማስተካከል በአሁኑ ጊዜ ሥራ ተቋራጩ የመጨረሻ ርክክብ ከማድረግ ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ የጥገና መሳሪያዎችን ሳይት ይዞ የገባ መሆኑን፡፡
- በስራ አስኪያጅ ቢሮ ያለው ፓርቲሽን በኮንትራት ሂደት ውስጥ የተዘለለ (Omition) እንደሆነ።

- በህንጻው ፊትና ኋላ ያሉት የአሉምኒየም በርና መስኮቶች ስፋት በሚሊሜትር ቢለያይም ያን ያህል የተጋነነ ችግር እንዳልሆነ፡፡
- መብራት መቆጣጠሪያው ከዋናው ሐይል መስመር ጋር በተገቢው ሁኔታ የተገናኘ ቢሆንም Proper grounding የለውም ስለዚህ ሥራ ተቋራጩ በተሰጠው Remark መሰረት በማስተካከል ላይ እንደሆነ። የደህንነት መፈተሻ መሽን የኤሌክትሪክ ሶኬት በቦታው አልተገጠመም የተባለው ግን በቦታው መኖሩን ለማስገንዘብ እንደሚወዱ፡፡ምናልባት በሲኪውሪት ምክነያት በጊዜያዊነት የፍተሻ መመርመሪያ መሳሪያው በገቢ መንገደኞች /arrival/ አቅጣጫ መቀመጡ ወደዚህ ድምዳሜ የወሰደ እንደሚመስላቸው፡፡
- ጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ግንባታ ከመሬት በታች ያለው ስራ ምልስ አፈር ላይ በመሆኑ የዲዛይን ለውጥ እንዲደረግ ይህንንም ተከትሎ ከመሬት በታች ያለው ሥራ በውለታ ከተያዘለት ወጪ ተጨማሪ ወጪ የወሰደ በመሆኑም አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ወጪ ከተያዘው በጀት በላይ እንዳይሆን በማሰብ አንዳንድ ስራዎችን ከብዛት በመቀነስ፣ አንዳዶቹን ተመሳሳይ አገልግሎት ሊሰጥ በሚችል በሌላ ማቴርያል በመተካት፣ አንዳንድ ስራዎችን ደግሞ ባለመስራት/omission አጠቃላይ ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ወጪ ለመገደብ ለመቆጣጠር እንደተሞከረ።
    - በዚሁም መሰረት የኃይል ማመንጫ ጄኔሬተር፣ የድምፅ ማጎልበቻ መሳሪያ፣ የሙቀት መቆጣጠሪያ፣ የአሳንሰር ሥራዎች በውለታው ውስጥ ቢኖሩም ከውለታው መዘለላቸው /Omission/ ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ መረጃዎችን ማያዛቸው፡፡ ይሁንና እነዚህን ሥራዎች ወደፊት እንደአስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል እንደሚሰሩ፤ ለምሣሌ በዚህ ዓመት የሙቀት መቆጣጠሪያ እና የማከፋፈል ሥራ በዕቅድ ተይዞ እየተካሄደ እንደሚገኝ።
- የአሳንሰር ስራው ከላይ በተገለፀው ምክንያት ያልተሰራ ቢሆንም ወደፊት የሚሰራ መሆኑን።
- በVIP ክፍል ውስጥ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በፋይናንስ እጥረት ያልተሟሉ መሆናቸው፣ በሂዳት ሁሉንም ለሚሟላት ጥረት እንደሚደረግ፡፡
- ቀደም ሲል ከላይ በተገጸው መሰረት(በዲዛይን ችግር ከመሰረቱ የግንባታ ወጭ መናር ጋር በተያያዘ) አንዳዶቹን ስራዎች ተመሳሳይ አገልግሎት ሊሰጥ በሚችል በሌላ ማቴርያል ዋጋቸውን ቀይሮ አዲስ ትዕዛዝ በመተካት ስራው እንዲከናወን መደረጉ፡፡ ከነዚህም መካከል የደረጃ መወጣጫና የመስኮት ክፈፍ ለውጥ እንደሚገኝበት፡፡ ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ መረጃዎችን ማያያዛቸው፡፡

<u>**በጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ግንባታ የጥበቃ ቤት የታዩ ችግሮች**</u>

- አብዛኛቹ የሽንት ቤት በሮች የሚሰሩ እንደነበሩ፡፡ ይሁንና በአጠቃቀም ችግር ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች በመሆናቸው ሊስተካከሉ የሚችሉ እንደሆኑ፡፡

<u>በጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ግንባታ የጀኔሬተር የውሃ ፓምፕ ቤት ላይ የታዩ ችግሮች</u>

የጄነሬተር ግዥ ሊያስከትል የሚችለውን የዋጋ ንረት በማሰብ እንዳይሰራ በድርታቸው የተወሰነ ሲሆን፤ የውሃ ፓምፑ ግን አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ፣

- **በውሃ መውረጃ በአፈር መደፈን ቢኖርም፤ ችግሩ በቀላሉ የሚስተካከል ስለሆነ የፐርፎረማንስ ችግር አድርጎ መውሰድ እንደማይገባ፣**
- **ከላይ እንደተገለጸው ጄነሬተሩ ስላልተሰራ የመስመር ገመዱ አለመገጠሙ፣ በተጨማሪም ገመዱ የኤሌክትሪክ ኃይል ስለሌለው ለአደጋ እንደማያጋልጥ ነገር ግን በገመድ አቀማመጥ ዙሪያ የታየው ችግር ጄኔሬተሩ ሲገጠም አብሮ የሚስተካከል እንደሆነ፣**
- **በ** remark **የተያዘ የሚስተካከል ግድፈት ቢኖረውም ችግሩ ግን የተባለውን ያህል አለመሆኑ።**
- **ጄኔሬተሩ ባይገጠምም የፓምፕ ክፍሉ ስለሚሰራ ህንፃው አገልግሎት እየሰጠ አይደለም ማለት እንደማይቻል፡፡**

<u>በጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ግንባታ በምድረ ግቢ ሥራና የመኪና ማቆሚያ ላይ የታዩ ችግሮች</u>

- **የመኪና ማቆሚያው አስፋልት ባንዳንድ ቦታዎች ውሃ የሚያቁርና በዚህም የተነሳ አንዳንድ ቦታዎች መፈራረስ ቢጀምሩም ሥራ ተቋራጩ የተበላሹትን ለማስተካከል እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ፡፡**
- **ከዚህ ምላሽ ጋር አባሪ ተደርጎ ከተያያዘው ማስረጃ ጋር እንደሚታየው በለውጥ ምክንያት**/omission/ **ውለታው ላይ ከነበሩት** 14 **መብራቶች ውስጥ** 6 **ብቻ እንዲሰሩ በመወሰኑ እንደሆነ፡፡**

ባህርዳር ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ የግንባታው ጥራት ደረጃን በተመለከተ

- **ያልተሸፈኑ የኮንክሪት ሥራዎች መኖር በሚፈለገው የጥራት ደረጃ አለመጠናቀቅ፣**
- **ሙሉ የወለልና የግድግዳ ሸክላዎችን መጠቀም በማይቻልበት ቦታ ላይ ጡቦች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት በሚፈለገው መጠን፣ ቅርጽና ጠርዞች ያለመስተካከል፣**
- **የመሬት ሸክላ ንጣፍ በተገቢው መንገድ ያለመነጠፍ፣**
- **የሲሚንቶ ሊሾ ሥራዎች በተፈለገው ጥራት ባለመሰራቱ ወጣገብነት ያለውና ውኃ ልኩን ጠብቆ አለመሠራቱ፣**
- **የኮርኒስ ፍሬሙ መስመሩን ጠብቆ ባለመቀረጡና ባለመገጠሙ ወጣገባነት መታየቱ ፣ማከፋፈያና መጋጠሚያ መስመሮችን በትክክል ከህንጻው መስመሮች ጋር ትይዩና ከወጣ ገባነት ፍጹም ነጻ አድርጎ መገንባት አለመቻሉ፡፡**

የተዘለሉ (የተሰረዙ) ሥራዎች በተመለከተ

- **ጀነሬተር፣ ትራንስፎርመርና የፓምፕ ቤቶች በውለታ ሰነዱ ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም ከዚህ ሥራ እንዲወጡ መደረጉ፣**

ባህርዳር ኤርፖርት ቀዝቃዛ መጋዘን በተመለከተ

- ህንጻው ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክፍሎች በፕላን ላይ ከተገለጸው ጋር ሲነጻጸር ቀጥሎ በተዘረዘረው ሰንጠረዥ መሠረት ልዩነት ያለው መሆኑ፣

የክፍሉ ስም	በውሉ ውስጥ የተገለጸ ርxወxከ /L*W*H/	የተገነባው ርxወxከ /L*W*H/
በረዶ ክፍል	12 x 9 x5.4ሜ	11.9 x8.30 x4.5ሜ
የማራገፊያ ክፍል	6 x 30 x5.4ሜ	5.84 x 29.20x4.5ሜ
ማቀዝቀዣ ክፍል ቁጥር 1	9 x 9 x5.4ሜ	8.85 x 8.3 x4.5ሜ
ማቀዝቀዣ ክፍል ቁጥር2	9 x 9 x5.4ሜ	8.85 x 8.3 x4.5ሜ
ማዘጋጃ ክፍል	30 x 21 x5.4ሜ	29.18x 20.75 x4.5ሜ
መጋዘን ክፍል	12 x 30 x7.20ሜ	11.90 x 29.15 x7.61ሜ

የባህርዳር ኤርፖርት ቀዝቃዛ መጋዘን ድጋፍ ሰጭ ቢሮ በተመለከተ

የተሠረዙና ያልተጠናቀቁ ሥራዎች

- የምድረ ግቢ የውሃ መስመር ሲስተም (በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት የታየ)
- የህንጻው ዋና የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ቦርድ(MDB) ከውጭው ዋና የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ቦርድ (CMDB) ጋር ያልተገናኘ መሆኑ (በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት የታየ)
- በመጸዳጃ ቤቶች ውስጥ የፕላስቲክ ፓርቲሽን ሥራዎች (በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት የታየ)
- 2350 x300 ሚሜ መጠን ያላቸው የMDF ሥራ (በግምት ክፍተቶችን ጨምሮ)
- ክሪስታል መስተዋት መጠን = 500 x400ሚሜ ብዛት=20
- ለጽዳት ሠራተኞች ማጠቢያ (ሲንክ)
- 30 ሜ.ኩ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ብዛት 2
- የፍሳሽ ማጣሪያ ጉድጓድ (soak away pit) በቁጥር 3
- የስልክ ሶኬቶች

የተገጠሙ ዕቃዎች ጥራትን በተመለከተ

- በአብዛኛው የተገጠሙት የማጠናቀቂያ እቃዎች (finishing materials) በውል ሰነዱ ውስጥ ከተቀመጠው ደረጃና ጥራት ጋር የማይጣጣሙ መሆናቸው፣ እነዚህም ዕቃዎች ሲንክ፣ የገላ መታጠቢይ ሳህን፣የእንጨት በሮች፣ የእጅ መታጠቢያ ሳህኖች፣የወለልና የግድግዳ ጡቦች፣ናቸው፡፡

- በድርብ የሸክላ ግንብ እንደሚገነቡ በውሉ ውስጥ የተጠቀሱት ፖሴቶች (Man holes) በትክክል ያልተሰሩ መሆናቸው፡፡

የሥራ ጥራትን በሚመለከት

- ጣራው በጥራት ሙሉ ለሙሉ ውኃ እንዳያፈስ ተደርጎ ባለመሰራቱ ምክንያት ፍሳሽ የተለያዩ የህነጻውን ክፍሎች በማበላሸት ላይ የሚገኝ መሆኑ፡፡

የዲዛይን ችግር

- MDF ፓርቲሽን በአንዳንድ ክፍሎች ውስጥ የተለያዩ የፓርቲሽን አይነቶች በመቀላቀላቸው ምክንያት የክፍሎቹን ውበትና እይታ ያበላሸው መሆኑ፡፡

የህንጻውን ዲዛይን በተመለከተ

- በህንጻው ጣሪያ ላይ ለብርሃን ማስገቢያ የተሠራው (sky light) የመስተዋት ግድግዳ ባላቸው ክፍሎች ውስጥ ያላስፈላጊ ሙቀት ማምጣታቸው፣
- በተጨማሪ በህንጻው ፊት ለፊት የተሠራው በረንዳ ምንም አይነት መጠለያ ሊሠራለት ስለማይችል አገልግሎት ላይ ሊውል የማይችል መሆኑ፣
- በመጨረሻ የህንጻው ጊዜያዊ ርክክብ ከተፈጸመ አንድ ዓመት አያለፈው ቢሆንም፣ በጊዚያዊ ርክክብ ወቅት የሳኒተሪ እና የኤሌክትሪካል ሥራዎች ባለመጠናቀቃቸው ተገቢው ፍተሻ ተደርጎ በኮንትራቱ መሰረት የዋስትና ጊዜ 365 ቀናት ውስጥ ሥራ ተቋረጩ በዋሰትና ጊዜ የተከሰቱ ችግሮችን ኃላፊነት ወስዶ የሚያስተካክልበት ሁኔታ በማመቻቸት የመጨረሻ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑ፡፡

49. **የኢትዮያ ኤርፖርቶች ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት ቢሮ ህንጻን በተመለከተ የተሰረዙ ሥራዎችን በተመለከተ**

- ፋውንቴን፣ ክሪስታል መሰተዋቶችና ጋልቫናይዝድ ባንቧዎች ከተሰረዙ ስራዎች መካከል መሆናቸው፡፡

ዲዛይንና ሰነድን በተመለከተ

- በአጠቃላይ የዚህ ፕሮጅክት ዲዛይን በEthiopian Building Proclamation No.624 May, 2009 ሲታይ ብዙ ጉድለቶች ይታዩበታል ለምሳሌ የሊፍት መጠን፣ የመጸዳጅ ቤቶች፣የአካለ ጉዳተኞች ታሳቢነትና የመሳሰሉት ክፍተቶች መኖራቸዉ፡፡

50. **የድርጅቱ የበላይ ሃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ ፡-**

<u>**የባህርዳር የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ በተመለከተ**</u>

- ግንባታው ያላለቀ ሥራ እና ግድፈቶቹ /Remarks/ ተለቅመው ስራ ተቋራጩ እያስተካከለ ባለበት ሰአት ስራው እንዳለቀ ተቆጥሮ ይህ ችግር አለ መባሉ ትክክል

አለመሆኑ፣ ባልተጠናቀቀ ስራ የተሰጠ አስተያየት ተገቢ አለመሆኑ፤ ድርጅታቸው በታዩ የአሰራር እና የጥራት ግድፈቶች ላይ ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በመሆን የቅርብ ክትትል በማድረግ ለሥራ ተቋራጩ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ገልጸዋል

- ጀኔሬተር ተዘሏል የተባለው ስህተት መሆኑን ቀደም ሲል ለኤርፖርቱ ሌላ ጀነሬተር የገባለት በመሆኑ ለባህርዳር ኤርፖርት የታሰበው ጀነሬተር ለመቀሌ ኤርፖርት ተዘዋውሮ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ፡፡

ባህርዳር ኤርፖርት ቀዝቃዛ መጋዘን በተመለከተ

- የተሰጡት መረጃዎች ባጠቃላይ በባለሞያ ስለመሰጠታቸው እንደሚጠራጠሩ፣ በመጋዘኑ የተተከሉ መሳሪያዎች በጣም የተወሳሰቡና ለመመርመርና ትክክለኝነታቸውን ለማረጋገጥ የተለየ ባለሞያ እንደሚያስፈልግ ከተገለጸ በኋላ የተከላና ተግባራዊ ሙከራ /Commissioning/ ሥራዎች በጣም በጥሩ ሁኔታ መከናወናቸው መግለጹ እርስ በርስ የሚጋጭ ሀሳብ መሆኑ፣ ባጠቃላይ በጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ፣ ባህርዳር ቀዝቃዛ መጋዘንና ደጋፊ ቢሮ ፣ የባህርዳር መንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ እና የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንጻ የተሰጡ የባለሞያ ግኝቶች እንደማቀበሏቸው፡፡
- ሆኖም የድርጅቱ የበላይ ሃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ ባጠቃላይ በጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ፣ ባህርዳር ቀዝቃዛ መጋዘንና ደጋፊ ቢሮ ፣ የባህርዳር መንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ እና የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንጻ ላይ የተሰጡ የባለሞያ ግኝቶች እንደማቀበሏቸው የገለጹ ሲሆን ነገር ግን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በባለሞያ ተሰርተው ከቀረቡት ግኝቶች በጋምቤላ መንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ ላይ ከተወሰኑ የባለሞያው ግኝቶች በስተቀር ግኝቶቹ ትክክል እንደሆኑ አምነው በወቅቱ ያጋጠሙዋቸውን አስገዳጅ ሁኔታዎች በመግለጽ እርምጃ እየወሰዱና ለወደፊቱም እንደሚወስዱ የገለጹ በመሆናቸው እና በዝርዝር በባለሞያ ለተሠጡ ግኝቶች በማስረጃ በማስደገፍ ትክክል አለመሆነቸው ማስረዳት ሲገባቸው በደፈናው እንደማይቀበሏቸው መግለጻቸው አግባብነት የለሌለው ነው፡፡

51. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በግንባታ ኮንተራት ውሉ መሰረት /Specification/ በተሟላ ሁኔታ እንዲገነቡ ባለመደረጋቸው ግንባታዎቹ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ እየተሰነጣጠቁ፣ ውሃ እያንጠባጠቡ ኮርኒሶቻቸው እየበሰበሱ ከመሆናቸው በተጨማሪ የተጠቃሚዎችን ምቾት የሚነሱ በመሆናቸው በድርጅቱ መልካም ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

ድርጅቱ የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድርበት ወቅት ያነሰ ዋጋ ብቻ መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ

52. ድርጅቱ የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድርበት ወቅት ያነሰ ዋጋ ያቀረበ ብቻ ከመምረጡ በፊት ያላቸው የማቴርያል፣የሰው ሀይል፣ የፋይናንስ አቅም እና መልካም ስም /የበፊት አፈፃፀም/ ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገበዋል፡፡

የድርጅቱ የህዝብ ግኙኝነትና ኮምንኬሽን ጽ/ቤት ሃላፊ የጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ህንፃ ግንባታን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በጥራት እንዳልተሰራና ኮርኒሶች የረገፉበት፣ በአሉሚኒየም ምትክ የቧንቧ ብረት የገባበት፣ የኤልክትሪክ ገመዶቹ በትክክል ያልተቀበሩበት እንደሆነና ይህን የገነባ ኮንትራክተር ተመልሶ የመቀሌ ግንባታ ስራ እንዲሰራ መሰጠቱ ኮንትራክተሮች በጨረታ በሚወዳደሩበት ወቅት ቅደመ ታሪካቸው ግምት ውስጥ የማይገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ ድርጅቱ በአብዛኛው ዝቅተኛ ዋጋን መሰረት ያደረገ መረጣ ስለሚደረግ ሥራ ተቋራጮች መስፈርቱን አሟልተው ቢገኙም፣ አፈፃፀም ላይ በርካታ ችግሮች እንደሚታይባቸው በ27/03/06 ዓ/ም በቁጥር AID 1/10 /280/06 ከኤርፖርት መሠረተ ልማት ዳይሬክቶሬት ከተገኘ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ ይንን ችግር ተረድቶ ጥቅምት 2004 ዓ/ም በወጣው የድርጅቱ የግዥ መመሪያ በአንቀፅ 20.21.3 ላይ የድህረ ብቃት ግምገማ ለማድረግ እና በ21.4.4 ላይ በጨረታ የሚወዳደሩ ተጫራቾች የድህረ ብቃታቸውን ለመመዘን እንዲያስችል ማቅረብ የሚገባቸውን ማስረጃዎች በዝርዝር መካተታቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

53. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግልጫ ላይ ሲመልሱ የሥራ ተቋራጮችን በጨረታ በሚያወዳድሩበት ጊዜ በሁለት ደረጃዎች ከፍለው እንደሆነ፣ የመጀመሪያው ቴክኒካል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ፋይናንሺያል መሆናቸውን፣ በመጀመሪያ ደረጃ የሥራ ተቋራጮች ያላቸውን የማሽነሪ አቅም፣ የሰው ኃይል፣ ወቅታዊ የፋይናንስ ሁኔታ፣ ባወጣነው የስራ መስክ ያላቸው ልምድ እንዲሁም ድርጅታችን ላወጣው ጨረታ የሚከተሉትን የሥራ አካሄድ/work methodology እንዲያቀርቡ በማድረግ ጥልቅ ግምገማ እንደሚያደርጉ፡፡ ይህም የተጫራቾችን የቴክኒክ አቅም ለማወቅ እንደሚያስችላቸው፡፡ በመቀጠልም ተጫራቾች የመጀመሪያ ደረጃ/ቴክኒካል ግምገማውን ካለፉ ወደ ሁለተኛው/ፋይናንሺያል ግምገማ እንደሚሸጋገሩና በሃገር ደረጃ የወጣውን የግዢ ደንብ መሰረት በማድረግ የቴክኒካል ግምገማውን ካለፉ ውስጥ ዝቀተኛ ዋጋ ያቀረበው አሸናፊ እንደሚሆን፡፡ በዚሁም መሰረት የጨረታ ሂደቱን እንደሚያናውኑና ከላይ እንደተገለጸው ዝቅተኛ ዋጋን ብቻ መሰረት ያደረገ አለመሆኑ ገልጸዋል፡፡

54. ይሁን እንጂ ድርጅቱ የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድርበት ወቅት ቅድመ ብቃት ግምገማ ካለፉት መካከል ያነሰ ዋጋ ያቀረበ ብቻ ከመምረጡ በፊት በድርጅቱ የግዢ መመሪያ የተቀመጡ የድርህረ ብቃት መገምገሚያ መስፈርቶች መሰረት ድርጅቶች

በመስራት ላይ ከሚገኙ የግንባታ ብዛት ጋር በማነጻጸር ሥራውን ለማከናወን በቂ የሰው ሀይል፣ ማሽነሪ፣ የማምረቻ መሳሪያዎች ባዛትና የተሟላ ኢንፍራስትራክቸር ያላቸው መሆኑን በአጠቃላይ ተጫራቾች የውል ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስችል በቂ የገንዘብ እና መልካም ስም /ዝና/ ግምት ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ በድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንጻ፣ በጋምቤላ መንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ፣ በመቀሌ አሉላ አባነጋ ኤርፖርት የቀዝቃዛ መጋዘን ደጋፊ ቢሮ፣ የባህርዳር ግንቦት 20 መንገዶኞች ማስተናገጃ ህንጻ ግንባታዎች ላይ የጥራት መጓደል፣ ከተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ በጀት በላይ እንዲወስዱ አድርጓል፡፡

በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች/ ህንፃዎች/ የውሃ አቅርቦት እና አሳንሱር በተመለከተ

55. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች/ ህንፃዎች/ በቂ የውሃ አቅርቦት፣ ሙሉ ስርጭት እና ውሃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ኤርፖርቶች የሽሬ ኤርፖርት የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ አቅርቦት እና ስርጭት የሌለው መሆኑ፣ ጋምቤላ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናደጃ ህንጻ የወሃ መስመር ዝርጋታ ቢኖረውም ኤርፖርቱ በጠቅላላ የውሃ ስርጭት የሌለው መሆኑ እንዲሁም በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለምአቀፍ ፣ መቀሌ፣ አክሱም፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጅማ ኤርፖርቶች በመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻዎች ውስጥ የውሃ አቅርቦት ቢኖረም ኤርፖርቶቹን ለመጠበቅ በዙሪያው ለሚገኙ የጥበቃ አባላት ምግባቸው ላመብሰል፣ ለመጠጥ እና ንጽህናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል በጥበቃ ማማዎች፣ በካምፖቻቸውና በምግብ ማብሰያ ኩሽናወቻቸው በቂ የውሃ አቅርቦት፣ የመስመር ዝርጋታ እና ስርጭት የሌለለ መሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡
57. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግልጫ ላይ ሲመልሱ በተገነቡት በአብዛኛው ኤርፖርቶች ውስጥ የውሃ አቅርቦት ሥራ ማሰራት በሚያስችል ሁኔታያለ መሆኑን ነገር ግን በሌሎች ደጋፊ ቢሮዎች አካባቢ በሂደት ወደፊት የሚሟላ መሆኑን ገልጸዋል።
58. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች/ ህንፃዎች/ በቂ የውሃ አቅርቦት፣ ሙሉ ስርጭት እና ውሃ ማከማቻ እንዲኖራቸው ባለመደረጉ ምክንያት በጋምቤላ ኤርፖርት በአጠቃላይ ውሃ ስርጭት የሌለ በመሆኑ በኤርፖርቱ የሚገኝ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የተገዛ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መኪና ከተገዛበት አላማ ውጪ ኤርፖርቱን አደጋ ላይ በመተው በደርሶ መልስ 34 ኪ/ሜ የኮረኮንች መንገድ በመጓዝ ከጋምቤላ ከተማ የመጠጥ ውሃ እንዲያመላልስ የሚደረግ መሆኑ እንዲሁም በናሙና በታዩ ኤርፖርቶች ውስጥ የሚሰሩ የጥበቃ አባላት ለመጠጥ፣ ምግባቸው ለማብሰልና ንጽህናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል የውሃ አቅርቦት ባለማግኘታቸው ምክንያት ስራቸው ላይ ጫና ከማድረሱ በተጨማሪ በተፈለገው መልኩ ንጽህናቸው እንዳይጠብቁ እንቅፋት ሊሆንባቸው ስለሚችል ዓለምአቀፍ መንገደኞች በሚያስተናግዱበት ወቅት በአገር ገጽታ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ ፡፡
59. ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር ከፍታ ያለው ማንኛውም ህንፃ አሳንሰር ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፡፡ አሳንስሮች ያለማቋረጥ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ ይኖሩባቸዋል፡፡

60. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር ከፍታ ያለው ማንኛውም ህንፃ አሳንሰር ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ስለመኖራቸውና አገልግሎት ስለመስጠታቸው ሲታይ፡-

- በድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ የሚገኘው አሳንሱር ህንፃው ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ አብዛኛው ጊዜ እንደማይሰራና አልፎ አልፎ በሚሰራበትም ወቅት በውስጡ ሰው እንዳለ ለብልሽት እንደሚዳረግ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ በቆየንባቸው 10 ወራቶች ተመልክተናል፡፡
- እንደዚሁም በቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት ተርሚናል ሁለት ውስጥ የሚገኝ ወደ ዲፓርቸር መግቢያ ያለው አሳንሱር /ሊፍት/ አገልግሎት መስጠት ካቆመ ሦስት አመት እንዳለፈውና ዕቃ ይዘው ለመግባትና ለመውጣት መቸገራቸውን በተርሚናል ሁለት ተከራይተው በመነገድ የሚገኙ የኢትዮጵያ ሆቴል እስካይ ሬስቶራንት ተወካይ ሃላፊ በተደረገላቸው ቃለ መለጠይቅ ገልጸዋል፡፡በተጨማሪ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሊፍቶችና ኤስካላቶሮች ላለፉት አስር ዓመታት ከታለመላቸው አገልግሎት አንፃር ተሟልተው ያልቀረቡበት ሁኔታ እንደነበር በ10/03/2006ዓ/ም በቁጥር AAB-03/458/06 ከድርጅቱ ለሲንቴክ ኃ/የተ/የግል ማህበር ተጻፈው ማስረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

61. ስለ ጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግልጫ ላይ ሲመልሱ በድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ የሚገኘው አሳንሱር በመጀመሪያ ጊዜ የኃይል/Power/ ችግር እንደነበረ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን አዲስ ትራንስፎርመር ለመትከል ረጅም ጊዜ እንደወሰደባቸው ከዚያ በኋላ ላለፉት ሁለት ወራት የነበሩ የሊፍት ችግሮችን በመቅረፍ በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት መስጠት የጀመረ መሆኑንና ችግሮችን በዘላቂነት ቀርፎ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

62. ይሁን እንጂ በድርጅቱ ዋና መ/ቤት ህንፃ እና ተርሚናል ሁለት ውስጥ የሚገኝ ወደ ዲፓርቸር መግቢያ ያሉት አሳንሱሮች /ለፍቶች/ በብልሽት ምክንያት የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ባለመስጠታቸው በመንገደኞች፣ በተከራዮችና በድርጅቱ ሰራተኞች የቀን ተቀን ስራ ላይ ተፅእኖ ከመፍጠራቸው በተጨማሪ ለአካል ጉዳተኞች አስቸጋሪና ምቹ እንዳይሆኑ አድርጓቿል፡፡

በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት በግንባታው ውል መሰረት ስራዎቹ ሙሉ በሙሉ ስለመሰራታቸው በሚመለከተው ባለ ሞያ ማረጋገጫ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ

63. በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት በግንባታው ውል መሰረት ስራዎቹ ሙሉ በሙሉ ስለመሰራታቸው በሚመለከተው ባለ ሞያ መረጋገጥ አለበት፡፡

64. ጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ፣ አዲስ አበባ ቦሌ የአሮጌው ኤርፖርት ጥገና፣ አዲስ አበባ ቦሌ የፖሊሶች መኖርያ ቤት፣ ዋና መ/ቤት ህንፃ እና የባህር ዳር የቀዝቃዛ መጋዘን ድጋፍ ሰጪ ቢሮ በግዚያዊ ርክክብ ወቅት በግንባታው ውል መሰረት ስራዎቹ ሙሉ በሙሉ ስለመሰራታቸው በሚመለከተው ባለ ሞያ ማረጋገጫ እንዲሰጥባቸው መደረጉ ከድርጅቱ በቀረበልን መራጃ ለመገንዘብ ተችልዋል፡፡

65. ማንኛውም የስራ ተቋራጭ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በሚገነባው ህንፃ ወይም የህንፃ አካል ላይ ለሚደርሰው የስራ ጥራት ጉድለት ተጠያቂነቱ ሳይቀር ጉድለቱን እንዲያስተካክል መደረግ አለበት፡፡

66. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩ በቦሌ ኤርፖርት አዲሱ የመንገደኞች ማስተናገጃ እና የፖሊሶች መኖሪያ ቤት ህንፃ ግንባታ ፣በጋምቤላ መንገዶኞች ማስተናገጃ ህንፃ፣ በባህርዳር መንገደኞች መስተናገጃ እና የቀዝቃዛ መጋዘኑ ደጋፊ ቢሮ ህንፃ ግንባታ እና በመቀሌ ቀዝቃዛ መጋዘንና ደጋፊ ቢሮ ህንፃ ግንባታ የታዩትን የጥራት መጓደሎች መንስኤ በመለየት ድርጅቱ በህንጻ ተቋራጮቹና በአማካሪ ማሃንዲሶች የወሰደው ህጋዊ እርምጃ ስለመኖሩ የሚያስረዳ ማስረጃ አልተገኘም፡፡

67.የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚና የመሰረተ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳሬክተር በቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስና በ10/04/06 በቁጥር PT-23/585/06 በተጻፈ የጨረታ እግድ ማስረጃ ለሳትኮን እና ለኮራኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበራት፣ ለኢቲጂ ዲዛይንና ኮንሰልታንት እና ለስለሺ አማካሪ አርኪቴክቶችና መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበራት ለሁለት አመት በድርጅቱ በሚያወጣው ማንኛውም ጨረታ እንዳይሳተፉ መደረጉንና ጉዳያቸው በቀጣይነት እንደሚታይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

68.ይሁን እንጂ ዘግይቶ የተወሰደው እርምጃ መልካም ጅምር ቢሆንም ጉዳዩ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጭምር ተልኮ ኮንትራክተሮችና አማካሪዎች ትምህርት ሊወስዱ በሚችሉበት ሁኔታ በሀገር አቀፍ ደረጃ Black List የሚደረግበትን ሥርዓት መፍጠር ይገባል፡፡

69. ሆኖም ማንኛውም የስራ ተቋራጭ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በሚገነባው ህንፃ ወይም የህንፃ አካል ላይ ላደረሰው የስራ ጥራት ጉድለት እንዲጠየቅና ጉድለቱን እንዲያስተካክል የማይደረግ ከሆነ ድርጅቱ በግንባታዎች የደረሱትን የጥራት ጉድለቶች ለማስተካከል የሚያወጣው ያልተገባ ወጪ በተጨማሪ ለወደፊቱ በሚያስገነባቸው የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በጨረታ አሸንፈው ግንባታቸው የሚከናውኑ የስራ ተቋራጮችና አማካሪ መሀንዲሶች በስራዎቻቸው በሚከሰቱ የጥራት መጓደሎች ምክንያት የሚደርስባቸው ምንም አይነት የተጠያቂነት ሁኔታ እንደሌለ አመላካች ስለሚሆን በሚያከናውኑዋቸው የግንባታ ስራዎች ግድየለሽ እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች የጥራት መጓደል እድላቸው ከፍተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ግንባታቸው የተጠናቀቁ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ መሰረተ ልማቶች ስርአትና፣ ቀጣይነት ባለው መንገድ፣ ጥገናና እድሳት እየተደረገላቸው መሆኑን በተመለከተ

70. ድርጅቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ሊኖረውና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ በማውጣት ጥገናና ዕድሳት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ እድሳት እየተደረገላቸው ስለመሆኑ ሲታይ፡-

- የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ብር 11.9 ሚሊዮን ወጪ በማድረግ ለኤርፖርት ፖሊሶች መኖርያ ህንጻ እ.ኤ.አ ሀምሌ 12 ቀን 2009 አስገንብቶ ያጠናቀቀ ሲሆን በ28/06/2005 ዓ/ም በኤርፖርት ፖሊሶች መኖሪያ ህንጻ የመስክ ጉብኝት ባደረግንበት ወቅት፡-
  - የህንጻው መወጣጫ መሰላል የሶስቱም ብሎክ በመርገጫ ብረቶች ላይ የተሞላው ስሚንቶ ተፈረካክሶ ብረቶቹም የሰዉን ክብደት መሸከም ስላልቻሉ መታጠፍ መጀመራቸውና ለተጠቃሚዎች ከፍተኛ አደጋ ሊያደርሱ እንደሚችሉ፣
  - የሶስቱም ብሎኮች የሽንት ቤት ጣርያዎች የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች ከፍተኛ ፍሳሽ ስላላቸው በአንዱ ሽንትቤት ወለል የሚፈስ ማንኛውም ፍሳሽ በቀላሉ ወደታች ስለሚያፈስ ፣እያንዳንዱ የሽንት ቤት ጣራ በስብሶ ፣ ሻግቶና አረንጓዴ አልጌ ማብቀሉ ፣
  - የሽንትቤቶቹ ፍሳሽ ከታች በኩል ግድግዳውን አልፎ የመተላለፍያ ኮሪደሮችን በቆሻሻ ውኃ መበከሉና ተጠቃሚውን ለበሽታ ሊዳርጉ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩ፣
  - በሰራዊቱ የመኝታ አልጋ በኩል የሚገኝ ግድግዳ ፍሳሽ ስለሚያስገባ ርሶ አልጌ ነገር ማብቀሉ፣
  - በሦስቱም ብሎኮች በጣም ከተወሰኑት በስተቀር አብዛኛው የሽንትቤቱ የእጅ መታጠቢያዎች ፣ የውኃ ሽንት መጠቀሚያዎች ፣ የሻወሮችና የዋናው ሽንት ቤት የውኃ መስመሮች አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው፣
  - በህንጻዎቹ የሚገኙ የሽንት ቤት በር ቁልፎች በሙሉ ከጥቅም ውጪ መሆናቸው፣
  - በየብሎኩ ማማ ላይ የተሰቀሉ የውኃ ታንከሮች የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው፣
  - የህንጻዎቹ የውጭ ግድግዳ በፍሳሽ ምክንያት መበላሸታቸው እና ግድግዳዎቹ መሰነጣጠቅ መጀመራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡
- የጋምቤላ ኤርፖርት አሮጌዉ ተንቀሳቃሽ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ የበርና የመስኮት መስታዉቶች የተሰባበሩ፣ ጣራዉ ውሃ የሚያንጠባጥብ፣ ኮርኒሶቹ እየበሰበሱና እየተቀዳደዱ እንደሚገኙ በመስክ ጉብኝት ወቅት በአካል ለማየት ተችሏል፡፡
- የጎንደር ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ ኮርኒሶቹ ዝናብ ከማስገባታቸው የተነሳ እየበሰበሱ መሆናቸው፣ በግንቡ በተለያዩ ዲዛይን የተለጠፉ ጡቦች እየረገፉና እየተፈረካከሱ መሆናቸው፣ የሻንጣ መረከቢያ እና መጫኛ ቦታ /በባጌጅ ኤርያ /ያሉ የህንፃው ምሶሶዎች በዕቃ መጫኛ ጋሪና ጋሪውን በሚጎትቱ ታጎች በየጊዜው እየተገጩ እተፈረካከሱ እና እየተሰነጣጠቁ ህንፃውን አደጋ ላይ እየጣሉት እንደሆነ፣ የድሮ የመንገዶኞች ማስተናገጃ ህንፃ በአሁኑ ሰአት የፌደራል ፖሊስ የጥበቃ አባላት የሚኖሩበት ሲሆን፣ ኮርኒሶቹ የበሰበሱ፣የተቀዳዱ፣ ግድግዳዎቹ የተሰነጣጠቁ፣ የሻገቱና የተቆፋፈሩና ጥገናና እድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑን የኦዲት ቡዱኑ በአካል ተገኝቶ ከማየቱ በተጨማሪ የኤርፖርቱ ስራ አስኪያጅ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡
- በስራ ላይ የሚገኘው የጂማ የመንገዶኞች ማስተናገጃ ህንፃ ኮርኒሶቹ በዝናብ ምክንያት የበሰበሱና የተቀዳደዱ በመሆናቸው ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ስለሚያንጠባጥቡ የመንገደኛውን ምቾት ከማጓደላቸው በተጨማሪ የውጭ ዜጎችም ተጠቃሚ ስለሆኑ በኤርፖርቱ ገፅታ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ቢሆንም ጥናት ተደርጎ በዕቅድ በጀት ተይዞለት ጥገና ያልተደረገለት መሆኑን በአካል

ጉብኝት እና የኤርፖርቱ የስራ ሃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ድርጅቱ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን በግንባታዎች ላይ የደረሱ ችግሮችን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የእድሳትና ጥገና ስራ አለማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

72. ስለጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ ያላቸው በጀትም ሆነ /resource/ ውስንነቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለያዩ ኤርፖርቶች ላይ የሚታዩትን ጉድለቶች እንደ አስቸኳይነታቸው ለማስተካከልና ጥገና ለማከሄድ እየተሞከረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

73. ሆኖም በድርጅቱ የሚገኙ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶ ቀጣይነት ያለው ዕቅድ በማውጣት ጥገናና ዕድሳት የማይደረግላቸው ከሆነ፣ መሰረተ ልማቶቹ ከሚጠበቅባቸው የአገልግሎት ዘመን ቀድመው የመፈራረስ እና በተጠቃሚዎቻቸው ላይ ጉዳት የማድረስ እድላቸው የሰፋ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የጥገናና የእድሳት ጊዜያቸው በተራዘመ ቁጥር የጥገናና የእድሳት ወጪያቸው ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡

ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን በተመለከተ

ድርጅቱ ያከራያቸው የኪራይ ቦታዎች በመመሪያው መሰረት የተቀመጠላቸው የኪራይ የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ድጋሚ ለጨራታ የሚቀርቡ ስለመሆናቸው በተመለከተ

74. ድርጅቱ ለመኪና ማቆሚያ በየሁለት ዓመቱ፤ ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረጥ ነፃ ሱቆች፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቅያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመቱ እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ መደረግ አለበት፡፡

75. ይሁን እንጂ፡-

- በጎንደር አፄ ቴዎድሮስ ኤርፖርት የሚገኙ የውጭ ማስታወቂያ አገልግሎቶች በ1995ዓ/ም ፔፕሲ ድርጅት፣ 1996 ዓ/ም ኮካኮላ ድርጅት ውል እንደፈፀሙ መረጃዎች ቢያመለክቱም፣ በድርጅቱ ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ መሰረት በየአምስት አመቱ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ በማገናዘብ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጡ አለመደረጋቸው ከኤርፖርቱ ባገኘነው የፅሁፍ ማስረጃ እና የኤርፖርቱ ስራ አስኪያጅ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ በተሰጠው መልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- እንደዚሁም ከ1995ዓ/ም እስከ 1998 ዓ/ም በድርጅቱ በቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት ተከራይተው እየነገዱ የሚገኙ 15 ተከራዮች ነሐሴ 05 ቀን 1995 ዓ/ም በቁጥር BIAA/7-58/2 ለሁሉም ተከራዮች በተጻፈ ደብዳቤ እና የካቲት 1999 ዓ/ም ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ

ምንጮች ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ መሰረት በየአምስት ዓመት ወይም ውልን ስለማቋረጥ በኪራይ ውሉ በተቀመጠው ማለትም 1ኛ የውል ዘመን ሲያበቃ፣ 2ኛ ውሉ አንደኛው ወገን ለሌላኛው ወገን በቅድሚያ የሁለት ወራት የስራ ቀናት ማስጠንቀቅያ በመስጠት በማንኛውም ምክንያት ውሉን ማቋረጥ፣ 3ኛ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ውል ሲጥስ የተካተቱን ማንኛውንም ግዴታ ካላከበረ ሌላኛው ወገን ውሉን ላላከበረ ወገን የአንድ ወር የስራ ቀናት ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወሉን ሊያቋርጥ ይችላል ተብለው ከተቀመጡት መሀከል ባንዱ ወይም ከዛ በላይ ባሉ ምክንያቶች ውሉን በማቋረጥ፣ እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ አለመደረጋቸው ከ1995 ዓ/ም እስከ 1998 ዓ/ም ከተከራዮች ጋር የተደረጉ ውሎችና በ2005 ዓ/ም የተደረገላቸውን የኪራይ ውል እድሳት ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ **ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ 3 ይመልከቱ፡፡**

76. ስለጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ በድርጅቱ መመሪያ መሠረት የውለታ ዘመናቸው የተጠናቀቁ ይዞታዎችን በ2003 ዓ/ም መጨረሻ ጨረታ የወጡ ቢሆንም ነባር ተከራዮች በጨረታ ለመወዳደር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሁከት ይወገድልን በማለት ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ክርክር እንዲያመራ በማድረጋቸው የጨረታ ሂደቱ እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

77. ይሁንና ለመኪና ማቆሚያ በየሁለት ዓመት፤ ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረፅ ነፃ ሱቅ፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቅያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመት እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣውን ጨረታ በተከራዮች ያልተገባ ክስ ምክኒያት በመቋረጡ ድርጅቱ ማግኘት የነበረበት ገቢ ከፍ እንዳይል ከማድረጉም ባሻገር ድርጅቱ በ1999 ዓ/ም ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር ያወጣው መመሪያ እና በአከራይና በተከራይ የተፈረመውን ህጋዊ የኪራይ ውል እንዲጣስና የህግ የበላይነት እንዳይተገበር አድርጎታል፡፡

በየአመቱ ስለሚደረግ የኪራይ አገልግሎት እድሳት በተመለከተ

78. ድርጅቱ ያከራያቸውን ነባር ይዞታዎች የውል ቆይታ ዘመን እስከሚያልቅ ድረስ በየዓመቱ የአገልግሎት እድሳት ማድረግ አለበት፡፡

79. በዚሁ መሰረት የመቀሌ ፣አክሱም፣ጎንደር፣ባህርዳር፣ጋምቤላ አርፖርቶች ያከራዩዋቸውን ነባር ይዞታዎች የቆይታ ዘመን እሰከሚያልቅ በየዓመቱ የአገልግሎት እድሳት እንደሚደረግላቸው ለኤርፖርት ስራ አስኪያጆች ባቀረብንላቸው ቃለ መጠይቅና የተከራዮች ፋይል ናሙና ወስደን በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ድርጅቱ የኪራይ ውሉ ዘመን ሲያበቃ ተከራይ በኪራይ የተረከበውን ባዶ ቦታ ወድያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንዲመልስና እንዲያስረክብ መደረጉን በተመለከተ

80. ድርጅቱ የኪራይ ውሉ ዘመን ሲያበቃ ተከራይ በኪራይ የተረከበውን ባዶ ቦታ ወድያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንዲመልስና እንዲያስረክብ ማድረግ አለበት፡፡

81. በዚሁ መሰረት የመቀሌ ፣አክሱም፣ጎንደር እና ባህርዳር የኪራይ ውሉ ዘመን ሲያበቃ ተከራይ በኪራይ የተረከበውን ባዶ ቦታ ወድያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንደሚያስረክብ ስራ አስኪያጆቹ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ተከራይ የኪራይ ውሉ ሳያከብር ሲቀር በመመሪያው መሰረት ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉን እንዲቋረጥ ስለመደረጉ በተመለከተ

82. ድርጅቱ ተከራይ የገባውን የውል ስምምነት ከጣሰ፣ ወይም የተከራየውን ይዞታ በንፅህና ካልያዘ፣ ተከራይ ውሉን ማቋረጥ ከፈለገ፣ ተመሳሳይ አሳማኝ ምክንያት በጽሑፍ ካቀረበ፣ ድርጅቱ ውል እንዲታደስ ለደንበኛው የውል እድሳት በጊዜ ገደብ አስታውቆ ምላሽ ካልሰጠው፣ ተከራይ በ3 ወራት ውስጥ የሚፈለግበትን ኪራይ አጠናቆ ካልከፈለ፣ ወይም ደርጅቱ ይዞታውን ለሌላ ተግባር ከፈለገው በነበረው ውል መሠረት ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉን እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡

83. ይሁን እንጂ ፡-

- የጎንደር አፄ ቴዎድሮስ ኤርፖርት የ2005 ዓ/ም ኪራይ ክፍያ መቆጣጠሪያ ቅፅ ጎህ ሆቴል ለቡዝ አገልግሎት በካ/ሜ ብር 8,000.00 ጠቅላላ ኪራይ በአመት ብር 72,000.00 የተከራየ ሲሆን፣ ከጥቅምት 12/ 2005 ዓ/ም እስከ ሰኔ 2005 ዓ/ም የ9 ወር ብር 72,000.00 አለመክፈላቸውና በመመሪያው መሰረት በ3 ወር የሚጠበቅባቸውን ክፍያ አጠናቀው ባለመክፈላቸው ውሉ እንዲቋረጥ አለመደረጉ በተጨማሪም ቅዱስ ጊዮርጊስ ማስታወቅያ ሰሌዳ ክፍያ ሳይፈፅም ሦስት ወር እንዳለፈው እና ውሉ እንዳልተቋረጠ ለኤርፖርቱ የስራ ሃለፊ በቀረበ መጠይቅ እና ከተከለሰ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል ፡፡
- እንዲሁም በድርጅቱ ያሉ ተከራዮች ከተፈቀደላቸው የንግድ አይነት ውጭ ዕቃዎች አቀላቅለው የሚሸጡ፣ በውሉ ከተቀመጠው ካ/ሜትር በላይ ቦታ አስፋፍተው የሚጠቀሙ እንዳሉ ጥቅምት 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም ዕቃ አቀላቅለው በሚሸጡትም ሆነ ትርፍ ቦታ ተጠቅመው በሚነግዱ ተከራዮች ኤሮኔቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ መሰረት ውላቸው እንዲቋረጥ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ በኦዲቱ ወቅት አልተገኘም፡፡

84. ስለጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ የጎንደር አፄ ቴዎድሮስ ኤርፖርት ጎህ ሆቴል በተመለከተ ኪራዩንና መቀጫውን ወዲያውኑ ማስከፈል አለመቻሉ እንደክፍተት የሚወሰድ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ተከራዩ ኪራዩንና መቀጫውን እንዲከፍል በማድረግ ውል እንዲያቋርጥ ተደርጓል፤

85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ውሉ መቼ እና እንዴት እንደተቋረጠ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

86. ድርጅቱ በአከራይና በተከራይ መካከል ያለውን የኪራይ ውል እንዲቋረጥ የሚያደርጉ ውል አለማክበሮች ሲከሰቱ ክትትልና ቁጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት ውሉ እንዲቋረጥ የማያደርግ ከሆነ ድርጅቱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ ከማድረጉም ባሻገር ተከራዮች ከድርጅቱ ተከራይተው እየሰሩባቸው የሚገኙ ቦታዎች እንደ ግል ይዞታቸው በመቁጠር የንግድ ሂደቱ ሊያዛቡት፣ ተገልጋዮች/መንገደኞች ከየኤርፖርቶቹ ማግኘት የሚገባቸውን አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዳያገኙ እና በአገልግሎቱ እንዳይረኩ በማድረግ በአገር ገፅታ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

በጨረታ መከራየት ያለባቸው የድርጅቱ የኪራይ ቦታዎች የጨረታ ህጉን ተከትለው እየተከራዩ ስለመሆናቸው በተመለከተ

87. ድርጅቱ ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች፣ ትናንሽ መጋዝኖች እና ሁለት ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶላቸው ተጨራቾች ላልቀረቡላቸው የኪራይ ይዞታዎች በስተቀር ሌሎቹን የጨረታ ህጉን ተከትሎ በጨረታ እንዲከራዩ ማድረግ አለበት፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ፤

- ለንደን ካፌ በ21/03/03 በቁጥር BIAA/7-54/3 በተጻፈ ደብዳቤ በመጀመሪያ የውል ስምምነት ላይ 109.9 ስኩ/ሜ. በአዲሱ ተርሚናል በጨረታ ያሸነፉበት ቦታ 2C2 ለስናክና ሬስቶራንት አገልግሎት የሚል መሆኑ ፣ሕዳር 08 /2003 ዓ.ም. በቁጥር PMD-8/05/03 በተጻፈ ደብዳቤ የቀረጥ ነፃ ሱቅ መደብር የውል ስምምነት ሳይኖራቸው ጊዜያዊ የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ቦንድድ መጋዘን 103 ካሬ ሜትር ቦታ መስጠቱ፣ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም. ድረስ 109.9 ካሬ ሜትር ቦታውን ይጠቀሙበት የነበረው ለስናክና ሬስቶራንት አገልግሎት ብቻ ሆኖ ሳለ ከሰኔ 29/ 2004 በቁጥር PMD- 8/22/04 በተጻፈ ደብዳቤ ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም. እስከ መስከረም 30 ቀን 2005 ድረስ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ ተብሎ የኪራይ ውል እድሳት መደረጉ፣
- ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በጨረታ አሸንፎ እ.ኤ.አ. July 24/2006 ውል የፈረመበትን 58.72 ካ.ሜ ይዞታ ለአልኮል መጠጦች መሸጫ አገልግሎት የተከራየው ቦታ ድርጅቱን ሳያስፈቅድ ይዞታውን ከተከራየበት ጊዜ አንስቶ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ አገልግሎት እየተጠቀመበት እንደሆነ የካቲት 21/1999 ዓ.ም ለኤርፖርቶች ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ በፃፈው ደብዳቤ ለመረዳት እንደተቻለና ድርጅቱ ተከራዩ ውሉን መጣሱ ገልጾ ህጋዊ እርምጃ መወሰድ ሲገባው ሐምሌ 1/1999 ዓ/ም የኮርፖሬት ማርኬቲንግ መምሪያ ኃላፊ አገልግሎቱን ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ በመለወጥ ለአንድ ዓመት ውሉ እንዲታደስ ማድረጋቸው እና እስከ አሁን ድረስ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- ዲና ልኡልሰገድ እ.ኤ.አ በ18/8/06 በጨረታ አሸንፈው ለቁንጅና ሳሎንና ማሳጅ አገልግሎ ውል የፈረሙበት 53.05 ካ.ሜ ይዞታ ለ4 ዓመታት በዚሁ የአገልግሎት ዘርፍ የውል እድሳት ሲከናወን የቆየ ቢሆንም ደንበኛዋ በ11/9/02 አዲስ የንግድ ፈቃድ በማውጣት ከተከራዩበት የንግድ ዘርፍ ውጪ ውሉን በመጣስ ዲና የተዘጋጁ ልብሶች መሸጫ በሚል የንግድ ዘርፉን ቀይረው እየሰሩ እንደነበር ፣ ይህ ይዞታ በ2003 ውል እድሳት የልብሶችና ጫማዎች ሱቅ ተብሎ የታደሰ መሆኑ በመጨረሻ በ2004 ውል እድሳት ደግሞ በተከለሰው ታሪፍ መሠረት የሀገር ባህል ልብሶች መሸጫ በሚል የታደሰ መሆኑን በ16/04/2006 ዓ/ም በቁጥር AUI-25/84/06 ከድርጅቱ የኦዲትና የአሰራር ጥራት ክትትል አገልግሎት በቦሌ ኤርፖርት ይዞታዎች ላይ ከተከናወነ የኦዲት ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፣
- የቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት የመንገደኞች መግቢያ ትኬት የጨረታ ሁኔታ በኦዲቱ ወቅት ሲታይ፤- የድርጅቱ ጨረታ ኮሚቴ ሚያዚያ 29 ቀን 2001 ዓ/ም የተደረገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር ኢ.ኤድጨኮ 225/ 101 መሠረት በቅድሚያ ኮሚቴው በጨረታ መክፈቻው ላይ ለተገኙ ተጫራቾች ስለተጨማሪ እሴት ታክስ የማብራሪያ ፅሁፍ እንደደረሳቸው ያረጋገጠ መሆኑንና በመቀጠልም ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች የተጨማሪ እሴት ታክስ **ሳይጨምር** በብር **4,510,000** የጨረታ ዋጋ ወስዶ እንዲሰራ ኮምቴው በሙሉ ድምጽ መስማማቱንና ለዋናው ስራ አስኪያጅ የውሳኔ ሃሳብ ያቀረበ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የመግቢያ ትኬት ሽያጭ ውሉ ላይ የተመለከተውን፣ በተከራይ ግዴታዎች ንዑስ አንቀፅ 2.1 ላይ በዓመት ብር **4,510,000** ተከራይ ለመክፈል መስማማቱን ተገልፆ በንዑስ አንቀጽ **2.4** ላይ ግን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይጨምር፤ በመንግስት የሚፈለጉ ማናቸውም አይነት ክፍዎች በሙሉ ለሚመለከተው የመንግስተት አካል መክፈል ያለበት እራሱ ተከራይ ተብሎ በመገለጹ ከጨረታ ኮሚቴ ውሳኔ ውጭ ድርጅቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል ተደርጓል፡፡ ከዚህ የተነሳ ድርጅቱ፡-
    - መክፈል ያልነበረበትን በተከራይ ስም የ9 ወር ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **441,195.66** / 49021.47 * 9/ ያለ አግባብ መክፈሉን በኦዲቱ ወቅት ከተገኙ ማስረጃዎች እና የቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት የፋይናንስ ቡድን መሪ እና የጨረታ ኮሚቴ አባል የሆኑት፤ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ የተጠቀሰውን ብር ያለ አግባብ ወጪ መደረጉ ለመረዳት ተችለዋል፡፡
    - በ2002 ዓ/ም ድርጅቱ በመግቢያ ትኬት ሽያጭ አገልግሎት ውል ማሻሻያ በማለት በአንቀጽ 2 በንዑስ አንቀጽ 2.1 ላይ ከጨረታ ኮሚቴው ውሳኔ ውጭ ተከራዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይጨምር ብር**4,510,000** እንዲከፍል መደረግ ሲገባው ወደ ብር **3,921,739.13** እንዲቀንስ ተደርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ድርጅቱ ከተከራዩ ማግኘት የነበረበትን ብር **588,260.87** እንዲያጣ እና ተከራዩ ያለ አግባብ ተጠቃሚ ማድረጉን በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ማስረጃዎች ከማመለከታቸው በተጨማሪ የቦሌ አለማቀፍ ኤርፖርት የፋይናንስ ቡድን መሪ እና ጨረታ ኮሚቴው አባል የሆኑት ስለትክክለኛነቱ ተጠይቀው ቅናሽ መደረጉ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ ተከራይ የንግድ ዘርፍ

የማያዋጣቸው ከሆነ በውሉ መሰረት ውላቸውን እንዲያቋርጡ ተደርጎ እንደ አዲስ ህጉን ተከትሎ ጨረታ እንዲወጣ መደረግ እንደነበረበት በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

- እንደዚሁም ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ከሚያስገኙ በክልል ኤርፖርቶች ከሚገኙ ተከራዮች በጎንደር አፄ ቴዎድሮስ በጨረታ 13 ያለጨረታ 31 ፣ በመቀሌ አሉላ አባነጋ በመነሻ ዋጋ 21፣ በጨረታ 3 ፣ በአርባ ምንጭ በመነሻ ዋጋ 6፣ በጨረታ 3 ፣ ባህርዳር ግንቦት 20 በመነሻ ዋጋ 40 ፣ በጨረታ 1፣ በላሊበላ በጨረታ 9፣ በድርድር 23 እና በአክሱም አፄ ዮሐንስ በመነሻ ዋጋ 36፣ በጨረታ 3 በድምሩ በጨረታ 32፣ ያለጨረታ 31 ፣ በድርድር 23 እና በመነሻ ዋጋ 103 በግንቦት ወር 2005ዓ/ም ለገበያ ልማት ዳይሬክቶሬት ከክልል ኤርፖርቶች አስተዳደር የተላኩ ማስረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁንና በጨረታ ተከራዩ የተባሉት ለተከራዮች ጥሪ የተደረገው በኤርፖርት አካባቢ በኮምፒዩተር በተጻፈ ጽሁፍ በመለጠፍ ተወዳዳሪዎች የተጋበዙ መሆኑ የተገለጸ በመሆኑ፣ ሁሉም የአካባቢ ህብረተሰብ በሚያየው ቦታ የተለጠፈ ስለመሆኑና ለስንት ቀናት እንደቆየ ለማወቅ አለመቻሉ፣ እንዲሁም በመንግስት ግዥ መመሪያ መሰረት በጋዜጣ እንዲወጡ ያልተደረጉ በመሆናቸው ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል በማያስችል እና ህግን ያልተከተለ መሆኑንን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

89.ስለጉዳዩ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሲመልሱ፡-

- ቀደም ሲል ስለቀረጥ ነፃ ንግድ አሰጣጥ በተገለፁ እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢዎች ሚኒስቴር ሐምሌ 10/1998 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በግልባጭ ለኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በፃፈው ደብዳቤ ስለቀረፅ ነፃ የሥራ መስክ ለመሰማራት የሚፈልግ ድርጅት ሚሟላት የሚያስፈልገው መስፈርት ሲገልፅ፣ **በዓለም አቀፍ የአየር ማረፊያ ተርሚናል ውስጥ የቀረፅ ነፃ መስጫ መደብር ሱቅ ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣** የአስመጪነት የውጭ ንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲሁም የክልል የንግድና እንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የችርቻሮ ንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው በመስኩ እንደሚሠማራ ይገልፃል፣ ድርጅቱ አስፈላጊው ፎርማሊቲ ስላሟላ የቀረፅ ነፃ የመንገድ ፈቃድ ከሚመለከተው አካል በመስጠቱ በዚሁ መሠረት የውል ዕድሳቱ ሊከናወንለት መቻሉን፣
- የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት የኪራይ ተመንን አስመልክቶ ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ/ም የድርጅቱ ማኔጅመንት የወሰነበት ቃለ ጉባኤ በተለይም በቃለ ጉባኤው ተራ ቁጥር 5 ላይ የድርጅቱን ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቻል የኪራይ ተመን ጭማሪና የውል እድሣተ ተከራዮች በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ አገልግሎት እየሰጡ ባሉበት የአገልግሎት ዓይነት መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆን በቃለ ጉባኤ የተወሰነ ሲሆን ይህንን መነሻ በማድረግ የውል እድሳቱ ተከራዩ በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ እየሠሩ ባለበት የቀረጥ ነፃ ሱቅ ሊታደስ መቻሉ፣
- በክልል ኤርፖርቶች አካባቢ የሚገኙት የንግዱ ማህበረሰብ በኤርፖርት ይዞታ ውስጥ የንግድ ቦታ እንዳለ በማህበረሰቡ ስለማይታወቅ ተከራዩች በኪራይ ጨረታ መነሻ ዋጋ እንዲከራዩ በማድረግ በንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅና እንዲኖራቸው የተደረገ ሲሆን

በአሁኑ ወቅት የንግድ እንቅስቃሴቸው እየተሻሻለ የመጡትን ኤርፖርቶች በጨረታ እንዲከራዩ መደረጉን። በተጨማሪም ኤርፖርቱን ለማስተዋወቅ ሲባል የማስታወቂያ ቦታዎች በመነሻ ዋጋቸው እንዲከራዩ መመሪያው ስለሚፈቅድ አብዛኞቹ የማስታወቂያ አገልግሎቶች መሆናቸው፣

- መመሪያው በጨረታ ለሚከራዩ ቦታዎች እንደስፈላጊነቱ በየአካባቢው የጨረታ ማስታወቂያዎችን በማውጣት በመለጠፍ በማወዳደር የሚችሉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

90. ይሁን እንጂ ተከራዮች **የቀረጥ ነጻ የንግድ ፍቃድ ለማግኘት አንዱ መስፈርት በዓለምአቀፍ የአየር ማረፊያ ተርሚናል ውስጥ የቀረፀ ነፃ መስጫ መደብር ሱቅ ያገኙ ስለመሆናቸው ሲረጋገጥ እንደሆነ ቢታወቅም፤** ተከራዮቹ ንግድ ፋቃዱ ከማግኘታቸው በፊት በድርጅቱ ለቀረጥ ነፃ ንግድ (Duty Free) ሱቅ ካወጣቸው ጨረታዎች ውስጥ **በህጋዊ መንገድ በማሸነፍ ውል ያልነበራቸው መሆኑ፣** እንዲሁም ማናጅመንቱ ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ/ም የድርጅቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ከመመሪያውና ከውሉ ውጪ ተከራዮች ውል ገብተው መነገድ ከነበረባቸው የንግድ አይነት ውጪ በሌላ ንግድ ቢሰማሩም በውል እድሳት ጊዜ አሁን እየነገዱበት በሚገኝ የስራ መስክ እንዲታደስላቸው በተወሰነው ውሳኔ ትርጉም አስጣጥና አተገባበር ላይ በተፈጠረው አለመግባባት ምክኒያት ታህሳስ 01/2005 ዓ/ም በተደረገው የማናጅመንት ስብሰባ ማናጅመንቱ ለሦስት የውሳኔ ሃሳብ የከፈለ እንደነበር፣ ከጠቅላላው በስብሰባው ከተገኙ አስራ አንድ አባላት ውሳኔ ሦስት ከሚደግፍ ሦስት የማናጅመነት አባላት በስተቀር የውሳኔ አንድና ሁለት የሚደግፍ ስምንት የማናጅመንቱ አባላት ሰኔ 29/2003 ዓ/ም ማናጅመንቱ በተጠጨባጭ እየሰሩበት ባለው ይታደስ ሲል መጀመሪያ የጨረታ አሸናፊ ሆነው በገቡበት ውል መሰረት ማለት እንደሆነና ይሰሩበት የነበረውን የንግድ አይነት በመለወጥ የተደረገው እድሳት ትክክል እንዳልነበር ከገለጹት ለመረዳት መቻሉ፤ እንዲሁም መመሪያና ውሉ ካለማስከበር ባሻገር በእድሳት ምክንያት ያለ ጨረታ ለነጋዴዎች የተሰጡ ቦታዎች ለጨረታ ቀርበው ቢሆን አሁን አስገኙት ከተባለው ጥቅም በላይ ሊያስገኙ የሚችሉበት ሁኔታ እንደነበር ግምት ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ የተሰጠው መልስ ተገቢ ነው ብለን አናምንም፡፡

91. ድርጅቱ ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች ትናንሽ መጋዝኖች እና ሁለት ጊዜ የጨረታ ማስታወቅያ ወጥቶላቸው ተጨራቾች ላልቀረቡላቸው የኪራይ ይዞታዎች በስተቀር ሌሎቹን የጨረታ ህጉን ተከትሎ በጨረታ እንዲከራዩ ባለማድረጉ ለሁሉም ተጫራች ተደራሽ በሆነ መልኩ በጋዜጣ ጨረታ አውጥቶ እንዲከራዩ ካልተደረጉት የንግድ የኪራይ ቦታዎች ማግኘት የነበረበትን ትክክለኛ ገቢ እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ በኤርፖርቱ አከባቢ በኮምፒተር በመጻፍ የተደረጉ የጨረታ ጥሪዎች በትክክል ተጽፈው ስለመለጠፋቸው፣ የት እና ለስንት ቀናት እንደተለጠፉ እና በትክክል ለተጫራቶች በእኩልነት ተደራሽ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የማያስችሉ በመሆናቸው አግባብ ያለው ሆኖ አልተገኘም ፡፡

በክልል ኤርፖርቶች በድርድር የሚከራዩ ቦታዎች በመመሪያው መሰረት የድርድር ኮሚቴው ቦታው ለተከራዩ ከማስረከቡ በፊት ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ ማስፀደቁን በተመለከተ

92. በድርድር የሚከራየው ቦታ በክልል ኤርፖርቶች ከሆነ ከስድስት ወራት እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ የኤርፖርት ሀላፊዎች የሚያቀርቡትን መነሻ መሰረት በማድረግ የድርድር ኮሚቴው ለተከራዩ ውል አዋውሎ ቦታው ከማስረከቡ በፊት ውሉ ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ ማስፀደቅ አለበት፡፡

93. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በመቀሌ አሉላ አባነጋ ኤርፖርት 3 እና በላሊበላ ኤርፖርት 23 የኤርፖርት ይዞታዎች በድርድር የተከራዩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ የመቀሌ ኤርፖርት ስራ አስኪያጅ ለተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የክልል ስራ አስኪያጆች በራሳቸው ማስፀደቅ እንዲችሉ የስልጣን ውክልና እንደተሰጣቸው ቢገልፁም የተሰጣቸው የስልጣን ውክልናው በድርድር ለሚከራዩ ሳይሆን በግልፅ ጨረታ ለሚከራዩ መሆኑንን ለክልል ኤርፖርት አስተዳደሮች በጥር 2004 ዓ/ም ከተሰጠው የስልጣን ውክልና ለመረዳት ተችሏል ስለዚህ በመመሪያው መሰረት ቦታው ለተከራዩች ከማስረከባቸው በፊት ውሉን ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርበው እንዲጸድቅ ሳያደርጉ ተከራዮች ስራ እንዲጀምሩ መደረጋቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

94. የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ የኤርፖርት አስተዳደሮች ከተሰጣቸው የስልጣን ውክልና በታች ለሆኑ የድርድር ቦታዎች ሂደቱን ለማሳጠርና ስራውን ለማቀላጠፍ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴዎች በሚያቀርቡት አስተያየቶች መሰረት ኃላፊዎች እንዲያጸድቁት የተደረገ ሲሆን ምንም እንኳ አሠራሩ በድርጅቱ ጥቅም ላይ ክፍተት ባይፈጥርም ይህ አካሄድ በነበረው መመሪያ መሠረት የተደገፈ ባይሆንም ይህን ለመቆጣጠር እንዲያመች ድርድሩ በሴንትራል [በገበያ ልማት ዳይሬክቶሬት በኩል] በወጣ የመነሻ ዋጋው መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ገልጸዋል።

95. በክልል ኤርፖርቶች ከስድስት ወራት እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ የኤርፖርት ሀላፊዎች የሚያቀርቡትን መነሻ መሰረት በማድረግ በድርድር የሚከራዩዋቸው ቦታዎች የድርድር ኮሚቴው ለተከራዩ ውል አዋውሎ ቦታው ከማስረከቡ በፊት ውሉ ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርበው እንዲጸድቁ ባለመደረጋቸው ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች መመሪያ ከመጣሱም በተጨማሪ በድርድር እንዲከራዩ የተደረጉ ቦታዎች መመሪያውን ተከትለው ስለመፈጸማቸው እና ለምን በግልጽ ጨረታ እንዲከራዩ እንዳልተደረጉ በሚመለከተው አካል ክትትልና ቁጥጥር እንዳልተደረገባቸው ያመለክታል፡፡

ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች ጥናት በማድረግ በየአመቱ ተመጣጣኝ ኪራይ ጭማሪ እየተደረገ ስለመሆኑ በተመለከተ

96. ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ መኖሩ ከብሔራዊ ባንክ ወይም

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ከተደረገ በተመጣጣኝ በየዓመቱ ኪራይ መጨመር አለበት፡፡

97. ይሁን እንጂ ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ መኖሩ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ከተደረገ በየዓመቱ በተመጣጣኝ ሁኔታ ኪራይ ስለ መጨመሩ የሚያሳይ መረጃ አላገኘንም፡፡

98. የኤርፖርቱ የበላይ ሃላፊ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ዘግይቶም ቢሆን በ2003 ዓ/ም የኪራይ ዋጋ ጭማሪ መደረጉን ገልጸዋል፤

99. ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ መኖሩ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ከተደረገ በየዓመቱ በተመጣጣኝ ኪራይ መጨመር እንደሚችል በመመሪያው የተቀመጠ ቢሆንም፤ ድርጅቱ በ10 ዓመት ውስጥ ዘግይቶ አንድ ግዜ ብቻ በማድረጉ እና ተከታታይነት ባለው የወቅቱን ፈጣን የዋጋ ግሽበት መሰረት በማድረግ የዋጋ ለውጥ ባለማድረጉ ማግኘት የነበረበትን ትክክለኛ አመታዊ ገቢ እንዳያገኝና ገቢው ከፍ እንዳይል አድርጓል፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ የሁኑትን የጥናት ግብአቶች መሰረት በማድረግ በየአመቱ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የኪራይ ማስተካከያ ካላደረገ ድርጅቱ ማግኘት የነበረበትን ተጨማሪ ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውልን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ

100. ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውልን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

101. ይሁን እንጂ፡-

- ተከራዮች የሚገለገሉበት ቦታዎች ስፋት መጠን ከድርጅቱ ጋር በተዋዋሉበት የአከራይ እና ተከራይ ውል መሠረትና በውሉ መሰረት መሆኑን ድርጅቱ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑ በቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት በተርሚናል አንድ /መናፈሻ/ እና በተርሚናል ሁለት /ዲፓርቸር በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት ተደርጓል፡፡ በተርሚናል አንድ /መናፈሻ/ በናሙና ከታዩት ስድስት ደንበኞች ከውሉ ውጭ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚገለገሉበት ቦታ በድምር 1822.41 ካ/ሜ እንደሆነና ድርጅቱ በአመት ብር 1,783,672.00 እያጣ መሆኑ፣ በተርሚናል ሁለት /ዲፓርቸር/ በናሙና ከታዩት ሰባት ደንበኞች ከውሉ ውጭ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚገለገሉበት ቦታ በድምር 145.58 ካ/ሜ እንደሆነና ድርጅቱ በአመት ብር 714,142 .10 ከሁለቱም ተርሚናሎች በናሙና ከታዩት ቦታዎች በዓመት በድምሩ ብር 2,497,814.80 እያጣ መሆኑ ለማረጋገጥ ትችሏል፡፡ **/አባሪ 4/**

- ድርጅቱ ለንደን ካፌና ሳተላይት ሬስቶራንት ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም 110 ካ.ሜ ባዶ የመጋዘን ቦታ በካሬ ሜትር በብር 1100.00 መከራየት ሲገባቸው በኪችን ዋጋ በካሬ ሜትር በዓመት ብር 812 ሂሣብ ተወስኖ ለ5 አመታት ፀንቶ የሚቆይ የኪራይ ውል በመፈራረሙ በዚህ ውሳኔ ምክንያትም ደንበኛው የመጋዘን ቦታን በኪችን ዋጋ ከተከራዩበት ቀን ጀምሮ የታሪፍ ክለሳ እስከተደረገበት እስከ ሰኔ 30/2003 ዓ.ም ድረስ በካ.ሜ በብር 1100 ሂሣብ እንዲከፍሉ ባለመደረጉ፣ ድርጅቱ ሊያገኝ ይችል የነበረው ብር 81,839.00 ማጣቱ በ16/04/2006 ዓ/ም በቁጥር AUI-25/84/06 ከድርጅቱ የኦዲትና የአሰራር ጥራት ክትትል አገልግሎት በቦሌ ኤርፖርት ይዞታዎች ላይ ከተከናወነ የኦዲት ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የኪራይ ተመን ለውጥ የተደረገ ቢሆንም ደንበኞች በኩሽና ኪራይ ዋጋ ላይ ለውጥ አለመደረጉ፣ ነገር ግን ቀደም ብሎ የኩሽና ኪራይ ተመን ብር 812 የሆነበት ምክንያት የዋናው ይዞታ (የሬስቶራንቱ) ተመንን በ2/3 በማብዛት (1218X2/3) ስለሆነ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የኩሽና ኪራይ ዋጋም የዋናው ይዞታ ታሪፍ 2/3 ሊሆን ሲገባው የገቢያ ልማት ዳይሬክቶሬት በጥናቱ ውስጥ ስላላካተተው ተግባራዊ አለመደረጉ፣ ይህ የኩሽና ይዞታ እንደሌሎቹ ይዞታዎች ሁሉ ታሪፍ ባለመስተካከሉ ምክንያት የሎው ስፖት እና ሎንደን ካፌና ሬስቴራንት የተባሉትን 2 ድርጅቶች ካሉት ውስጥ ቢታዩ ድርጅቱ በ2004 በጀት ዓመት ብቻ ሊያገኘው ይገባ የነበረ ብር **221,990.76** ገቢ እንዳጣ በ16/04/2006 ዓ/ም በቁጥር AUI-25/84/06 ከድርጅቱ የኦዲትና የአሰራር ጥራት ክትትል አገልግሎት በሸኝ ደብዳቤ የተላከ በቦሌ ኤርፖርት ይዞታዎች ላይ ከተከናወነ የኦዲት ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በሌላ በኩል የታሪፍ ክለሳ ተግባራዊ የተደረገው ከሐምሌ 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ ቢሆንም የለንደን ካፌና ሬስቶራንት 103 ካ.ሜ ይዞታ በአዲሱ ታሪፍ መሠረት ውል የታደሰው ከህዳር 1/2004 እስከ ጥቅምት 30/2005 በመሆኑ በአዲሱ ታሪፍ ለካሬሜትር ብር 4100 መሠረት ሊከፍሉበት የሚገባው የ103 ካ.ሜ ቦታ ለ4 ወራት በቀድሞው ታሪፍ ብር 1100 ሂሣብ በመታደሱ ድርጅቱ ሊያገኘው ይገባ የነበረ ብር 12,000 እንዳጣ በ16/04/2006 ዓ/ም በቁጥር AUI-25/84/06 ከድርጅቱ የኦዲትና የአሰራር ጥራት ክትትል አገልግሎት በሸኝ ደብዳቤ የተላከ በቦሌ ኤርፖርት ይዞታዎች ላይ ከተከናወነ የኦዲት ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ድርጅቱ ይዞታዎችን ሲያከራይ ደንበኞች በይዞታዎቹ ላይ ጉዳት ቢያደርሱ ለማስተካከያ የሚሆን ገንዘብ (Pledge) ውል ሲፈርሙ ወይም ኮንትራታቸው ሲታደስ እንዲያስይዙ የሚያስገድድ ቢሆንም ጉዳዩ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ የተወሰኑ ተከራዮች ማስያዝ ካለባቸው የገንዘብ መጠን ያነሰ እንዲያስይዙ ሲፈቀድ ሌሎች ደግሞ ከነጭራሹ ሳያስይዙ በመቆየታቸው ታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም መጨረሻ በተወሰደ መረጃ መሠረት ከ2 ሚሊዬን ብር በላይ በወቅቱ መያዝ የነበረበት የመያዣ ገንዘብ መኖሩን በ16/04/2006 ዓ/ም በቁጥር AUI-25/84/06 ከድርጅቱ የኦዲትና የአሰራር ጥራት ክትትል አገልግሎት በሸኝ

ደብዳቤ የተላከ በቦሌ ኤርፖርት ይዞታዎች ላይ ከተከናወነ የኦዲት ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

102. የኤርፖርቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ፡-

- በተርሚናል 1 ፊት ለፊት መናፈሻ አካባቢ ለሚገኙት ካፌና ሬስቶራንቶች በወቅቱ ቦታዎችን የተከራዩት ለቤቱ ብቻ እንዲከፍሉና ሌላውን ክፍት ቦታ እንዲጠቀሙበት ታሳቢ ተደርጐ እንደነበር፣ ሆኖም አሁን ኪራይ እየከፈሉ ካለው ይዞታ ውጪ እየተጠቀሙበት ላለው ተጨማሪ ይዞታ ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያስችል ጥናት የተካሄደ ቢሆንም ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እያሉ ቦታዎቹ የሚፈርሱ በመሆኑ ለጊዜው ተግባራዊ ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣ እንዲሁም
- በተርሚናል 2 ዲፓርቸር በኪራይ ውል ከያዙት ቦታ ውጭ እየተጠቀሙ የሚገኙትን ተከራዮች በተመለከተ ይዞታዎቹ ለተወሰኑት Open Space ላይ የተከራዩ በመሆኑ እና ቦታው የተከለለ ባለመሆኑ የተወሰነ ወጣ ገባ በመኖሩ እንዲሁም ቦታው ለሌሎች ተከራዬች የሚከራይ አለመሆኑና ከኦፕሬሽንና ከመንገደኞች ፍሰት አንፃር ተፅዕኖ ካልፈጠረ ተከራዬቹ ፈቃደኛ ሆነው ከተገኙ ተጠይቀው ለተጨማሪ ይዞት እንዲከራዩ ማስተካካያ ተደርጐ የድርጅቱን ጥቅም እንዲያስጠብቅ የተደረገ እንጂ ቦታውን በተከራዩበት ወቅት አስፋፍተው የያዙት አለመሆኑን ገልጸዋል።

103. ሆኖም በተርሚና ሁለት በዲፓርቸር ውስጥ የሚነግዱ ተከራዮች ከላይ በተገለጸው በተቃራኒ በመንገደኞች መተላለፊያ ቦታ ላይ የንግድ እቃዎቻቸው ወይም ወንበርና ጠረጴዛ ዘርግተው ያለ ምንም ክፍያ እየተጠቀሙ ስለመኖራቸው በአካል ጉብኝት ባደረግንበት ወቅት የተደረገ ልኬት ስለሆነ የተሠጠው ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

104. በአከራይና በተከራዮች መሀከል የተፈረሙ ውሎች ተግባራዊ ባለመደረጋቸው እና በመጣሳቸው ምክንያት ድርጅቱ ማግኘት የነበረበትን ትክክልኛ ገቢ እንዳያገኝና ጥቅሞቹን በተለያዩ ሁኔታዎች እንዲያጣ ከማድረጋቸውም፣ ተከራዮች የተከራዩትን ቦታ በፈለጉት ጊዜ፣ ለፈለጉት አገልግሎት ስለሚያውሉት የኤርፖርቱ የገበያ መመጣጠን ስለሚያዛባው የተጠቃሚዎች/የመንግደኞች ፍላጎት እንዳይሟላና በንግድ አገልግሎቱ እንዳይረኩ ስለሚያደርገው ድርጅቱ ማግኘት የነበረባትን ገቢ ዝቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

105. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

106. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ

የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ስለመዘርጋቱና ስለተግባራዊነቱ ሲታይ፡-

- አንድ የአውሮፕላን ማረፊያ አገልግሎት ለመስጠት የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልገሎት በዋነኛነት እንደሚያስፈልግ ቢታወቅም ኤጀንሲው በኤርፖርቶች ድርጅት እቅድ ዝግጅት ውስጥ ተሣተፎ እንደሌለው፣ የአውሮፕላን ጣቢያን ዲዛይን ለማድረግ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ከመሰረታዊና ወሳኝ ጉዳይ አንዱ መሆኑን ድርጅቱ ግምት ውስጥ የማያገባው መሆኑ፣

- የአውሮፕላን ማረፊያዎች ግንባታዎች ሲታቀዱ ኤጀንሲው ባለመሳተፉ በአውሮፕላን ማረፊያው ላይ ለሚፈለገው የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት፣ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ መሣሪያዎችና የመገናኛ አውታሮችን ለመዘርጋት የሚያሰፈልግ ቦታ፣ ለሥራ ምቹ የሆነ ቢሮና የሚመደበው (የሚያስፈልገውን) የሰው ኃይል በቅድሚያ ባለመታወቁ የመገናኛና መሣሪያዎቹን ለመትከል የሚያሰፈልጉ ግብዓቶች (የኤሌክትሪክ ኃይል አለመሟላት) ከአውሮፕላን ማረፊያው ደረጃ ጋር የተጣጣሙ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎችና ሲስተሞች ፣ የሰው ኃይል በቁጥርም ሆነ በሚፈለገው አገልግሎት አንፃር ለማዘጋጀትና ለመመደብ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ በጅንካ፣ በአዋሣ፣ በባሌ ሮቤ፣ በሰመራና በኮምቦልቻ የአውሮፕላን ማረፊያዎች እየተገነቡ ቢሆንም የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዐቶችን ለማዘጋጀት መረጃ አለማግኘታቸው ለዚህ ማስረጃ እንደሆነ ፣
    - ለአራት መጋቢ አውሮፕላን ጣቢያዎች (አክሱም፣ አሶሳ፣ ጅጅጋና ጋምቤላ) አዲስ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ሲስተም (የንፋስ ፍጥነትና አቅጣጫ፣ የአየር ግፊት መሣሪያ፣ የአየር ሙቀትና ምዘና፣ የአየር እርጥበት) ወደፊትም ተጨማሪ ሴንሰር ሊገጠምበት የሚችል በ2004 ዓ.ም ከውጭ ሀገር ቢመጣም በመጋቢ ኤርፖርቶቹ የአውሮፕላን ማኮብኮቢያ ሜዳ አቅራቢያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለማግኘት ባለመቻሉ ተከላው መዘግየቱና ኤጀንሲያቸው የኤሌክትሪክ ኃይል ለመዘርጋት ተጨማሪ ሥራ፣ ወጪና ጊዜ ማስከተሉ ፣
    - በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ ባለድርሻና ተባባሪ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ አለመፈጠሩ በአለም አቀፍና በሀገር ደረጃ በፍጥነት እያደገ ለመጣው የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት አለመቻሉ ለምሳሌ፡-
        - አዳዲስ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ሲገነቡም ሆነ ነባሮቹ ሲስፋፉ ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት መረጃ ባለመገኘቱ የአዲስ አበባ ቦሌ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲስፋፋ በፕሮጀክተ ቁጥር PRJ-No: 20467 ከሲመንስ ኩባንያ የሰው አልባ የአየር ሁኔታ መከታተያ ሲስተም ግዥና ተከላ በ3ሚሊዮን ብር ዋጋ ሲከናወን **ከኤጀንሲያችን ጋር በምክክር ባለመሰራቱ ምክንያት** ከመነሻው ጀምሮ ሲስተሙ አገልግሎት ሊሰጥ ባለመቻሉ ኤጀንሲያችን በ2006 በጀት ዓመት ሌላ ሲሰተም ለመትከል በግዥ ሂደት ላይ መሆኑ ፣ በተጨማሪም እንደ ባለ ድርሻ አካል ኤርፖርቶች ሲስፋፉም ሆነ አዳዲስ ሲገነቡ ከዕቅድ እስከ ግንባታ ምንም መረጃ እንዲኖረን ባለመደረጉ የጅማ ኤርፖርት ሲስፋፋ ወደ አንድ ሚሊዮን ብር ወጪ

የተደረገለት የዲጂታል ዊንድ መማሪያ ተተክሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲነሳ መደረጉ፡፡

- የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ባለድርሻ አካላቶችን በመሰብሰብ እንዲወያዩ ስለማድረጉ መረጃ እንደሌላቸው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዮሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡
- በናሙና ከታዩት ኤርፖርቶች መቀሌ፣ አክሱም፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጅማ እና ጋምቤላ ድርጅቱ ኤርፖርቶችን የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን በተመለከተ ከክልል ኤርፖርቶች ጋር በዕቅድ የተመራ መደበኛና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ለክልል ኤርፖርት ስራ አስኪያጆች ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እና የክልል ኤርፖርቶች መዋቅር በማየት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- አዳዲስ ተከራዮች ሲኖሩና አመታዊ የኪራይ ውል እድሳት ሲኖር መደበኛ ባልሆነ መልኩ ክልል ኤርፖርቶች መረጃ የሚልኩ ቢሆንም ድርጅቱ ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራ፣ መደበኛና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርአት ያልዘረጋ መሆኑ ለክልል ኤርፖርት ስራ አስኪያጆች ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

107. የኤርፖርቱ የበላይ ሃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ የድርጅቱ መሰረተ ልማት ግንባታዎችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶች ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን፣ ከባለድርሻ አካለት ጋር በእቅድ የተመራ መደበኛ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እነደ ድርጅት ለመተግበር እየተሰራበት እንደሚገኝ እንዲሆም ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ተዘርግቶ እየተተገበረ እንደሆነ ገልጸዋል።

108. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ከክልል ኤርፖርት አስተዳደሮች እና ከድርጅቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ቃለ መጥቅ እና በተከለሱ ማስረጃዎች መደበኛ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርአት አለመዘርጋቱ ለመረዳት በመቻሉ የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

109. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆኑ ባለማድረጉ በገነባቸው እና በሚገነባቸው መሰረተ ልማቶች የጥራት መጓደል እንዲከሰት፣ በተያዘላቸው ጊዜና ገንዘብ እንዳይጠናቀቁ፣ ኤርፖርቶቹ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዳይሆኑ፣ ኤሮኔቲካል ካልሆኑ የገቢ ምንጮች ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዳያገኝ እና የተጠቃሚዎችን እርካታ እንዲቀንስ አድርጓል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳቦች

110. ድርጅት የሚገነባቸው መሰረተ ልማቶች ግንባታና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፡፡ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ አላማ አንጻር በመሰረተ ልማቶች ግንባታና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደር አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ብቃት እና ውጤታማነት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

111. ድርጅቱ ዘግይቶም ቢሆን የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት እንዲያስችለው የመቋቋሚያ አዋጁና ደንቡ እንዲሻሻልለት ያጋጠሙትን ችግሮ በጥናት አስደግፎ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በእንቅስቃሴ ላይ ቢገኝም በወቅቱ እንዲሻሻልለት አላደረገም ፡፡

112. ድርጅቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የግንባታ መመሪያዎች ቢጠቀምም መቋቋሚያ ደንቡን መሰረት ያደረገ እና የድርጅቱን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የራሱ የግንባታ የአፈፃፀም መመሪያ አላወጣም፡፡

113. ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የካቲት 1999 ዓ/ም የወጣው መመሪያ ቢኖርም በስራ ላይ በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ ክፍተቶች ያሉት በመሆኑ ድርጅቱ ጥናት አድርጎ ክፍተቶችን ለማስተካከል በሂደት ላይ ቢገኝም ድርጅቱ በዚህ ዘርፍ የተፈጠሩ ከፍተኛ ችግሮች በወቅቱ ለመፍታት ያስችለው ዘንድ መመሪያው በወቅቱ እንዲሻሻል አላደረገም፡፡

114. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ እና የተሟላ የሰው ሃይል የለውም፡፡

115. በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የመልካአ ምድራዊ አቀማመጥ ወዘተ መሰረት ያደረገ የአዋጭነት ጥናት አልተደረገላቸውም፡፡

116. ድርጅቱ ከሚየስተዳድራቸው አስራ ሰባት ኤርፖርቶች ውስጥ ስምንት ኤርፖርቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /Title Deed/ ፣ አስራ ሁለት ኤርፖርቶች የመሬት አጠቃቀም ፕላን/Land use plan/ እና መሪ ዕቅድ/Master Plan/ የላቸውም፡፡

117. በድርጅቱ የተገነቡ እና በመገንባት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ ከተያዘላቸው ገንዘብ ከብር 3,151,187.27 /15%/ እስከ ብር 17,936,899.42 /34%/ እና ጊዜ ከ65 /15%/ ቀን እስከ 559 /266%/ ቀን በላይ ወስደዋል፡፡

118. በድርጅቱ በናሙና ከታዩ አብዛኞቹ ግንባታቸው የተጠናቀቁ የድርጅቱ መሰረተ ልማቶች በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ በመለየት እና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ጊዚያዊ ርክክብ ከተደረገላቸው ቀን ጀምሮ በ365ኛው ቀን ጠብቆ የመጨረሻ ርክክብ አያደርግም፡፡

119. በናሙና የታዩ ሁሉም በኤርፖርቶች ውስጥ የሚገኙ አይሮፕላኖች፣ መንገዶኞች እና ሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነታቸው ለመጠበቅ የሚያስችል በተሟላ መልኩ የዙሪያ አጥር፣ ደረጃው የጠበቀና በቂ የጥበቃ ማማ፣ አገልግሎት የሚሰጥ የለሊት የዙሪያ አጥር መብራት፣ ጥራቱ የጠበቀ አገልግሎት የሚሠጡ የፍተሻ ማሽኖች፣ ለሚያርፉና ለሚነሱ አውሮፕላኖች የተሟላ የሜትሮሎጂ አገልግሎት እና የእሳት አደጋ ማጥፊያና መከላከያ የላቸውም፡፡

120. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች **በተሟላ መልኩ** በግንባታ ኮንትራት ውል ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ መሰረት ግንባታቸው አይጠናቀቅም፡፡

121. ድርጅቱ የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድሩበት ወቅት ቅድመ ብቃት ግምገማ ካለፉት መካከል ያነሰ ዋጋ ያቀረበ ብቻ ከመምረጡ በፊት፤ ተጫራቾቹ እያከናወንዋቸው ከሚገኙ የግንባታ ብዛት ጋር በማነጻጸር ሥራውን ለማከናወን በቂ የሰው ሀይል፣ ማሽነሪ፣ የማምረቻ መሳሪያዎች ብዛታቸው የተሟላ ያላቸው መሆኑን እና ተጫራቾች የውል ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስችል በቂ የገንዘብ እና መልካም ስም /ዝና/ ያላቸው ስለመሆኑ አላረጋገጠም፡፡

122. በናሙና በታዩት በድርጅቱ የተገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች /ህንፃዎች/ በቂ የውሃ አቅርቦት እና የተሟላ ስርጭት የላቸውም፡፡

123. በድርጅቱ የተገቡና ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር ከፍታ ያላቸው ህንጻዎች አሳንሰር ቢኖራቸውም አሳንስሮች ያለማቋረጥ አገልግሎት እየሰጡ አልተገኙም፡፡

124. በድርጅቱ ግንባታቸው በተጠናቀቁና በሂደት ላይ በሚገኙ መሰረተ ልማቶች ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት በስራ ተቋራጮች እና በአማካሪ መሀንዲሶች ለደረሱ የስራ ጥራት ጉድለቶች ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በግንባታ ጥራትና መዘግየት ተጠያቂ ናቸው ላላቸው ስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ድርጅቱ በሚያወጣቸው የግንባታ ጨረታዎች እንዳይሳተፉ ማገዱ መልካም ጅምር ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ጉድለቶች እንዲያስተካሉ አልተደረገም፡፡ እንዲሁም ጉድለቱን ያደረሱ አካላት በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የተደረገ ጥረት የለም፡፡

125. ድርጅቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች ሙሉ በሙሉ የቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ቀጣይነት ያለው ዕቅድ በማውጣት ጥገናና ዕድሳት እያደረገላቸው አልተገኘም፡፡

126. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረፅ ነፃ ሱቅ፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ

ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቅያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመት እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ ለማድረግ ጨረታ ቢወጣም ተከራዮች ባነሱት ክስ ምክንያት ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

127. ከመልካም ስራዎች መካከል ድርጅቱ ያከራያቸውን ነባር ይዞታዎች የውል ቆይታ ዘመን እስከሚያልቅ ድረስ በየዓመቱ የአገልግሎት እድሳት እንደሚደረግላቸው ታይቷል፡፡

128. ከመልካም ስራዎች መካከል ድርጅቱ የኪራይ ውሉ ዘመን ሲያበቃ ተከራይ በኪራይ የተረከበውን ባዶ ቦታ ወድያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንዲመልስና እንዲያስረክብ አድርጓል፡፡

129. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ድርጅቱ ተከራይ የገባውን የውል ስምምነት ከጣሰ፣ ወይም ተከራይ በ3 ወራት ውስጥ የሚፈለግበትን ኪራይ አጠናቆ ካልከፈለ፣ ወይም ድርጅቱ ይዞታውን ለሌላ ተግባር ማዋል ከፈለገ በነበረው ውል መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ጥሰው በተገኙ ተከራዮች ላይ ውላቸው እንዲቋረጥ እያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

130. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ድርጅቱ ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች ትናንሽ መጋዝኖች እና ሁለት ጊዜ የጨረታ ማስታወቅያ ወጥቶላቸው ተጨራቾች ላልቀረቡላቸው የኪራይ ይዞታዎች በስተቀር **በአብዛኛው** ሌሎቹን የጨረታ ህጉን ተከትለው በጨረታ እንዲከራዩ አልተደረጉም፡፡

131. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ድርጅቱ በክልል ኤርፖርቶች በድርድር የሚከራዩ ቦታዎች ከስድስት ወራት እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ የኤርፖርት ሀላፊዎች የሚያቀርቡትን መነሻ መሰረት በማድረግ የድርድር ኮሚቴው ለተከራዩ ውል አዋውሎ ቦታው ከማስረከቡ በፊት ውሉ ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ እንዲፀድቁ አልተደረጉም፡፡

132. ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ ያስገባ፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ መኖሩ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ስለመኖሩ በማየት በ10 ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ ያደረገ ቢሆንም ተከታታይነት ባለው መልኩ እና ተመጣጣኝ ኪራይ እንዲጨመር አላደረገም፡፡

133. ድርጅቱ በአከራይ እና ተከራይ መካከል የተቀመጡ ውሎች **በተሟላ መልኩ** ተግባራዊ እያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

134. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት አልዘረጋም፡፡

ክፍል አራት

ማሻሻያ ሀሳቦች

135. ድርጅቱ የሚያከናውናቸውን ስራዎች፣ ሀላፊነቶች፣ ያጋጠሙትን ችግሮች በማጥናት እና በመለየት የመቋቋሚያ ደንቡ እንዲሻሻልለት ለማድረግ የተጀመረው ጥረት በማፋጠን ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እንዲፀድቅ ቢያደርግ የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት ያስችለዋል፡፡

136. የድርጅቱን የመቋቋሚያ ደንብ መሰረት በማድረግ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የግንባታ መመሪያዎች እና ተሞክሮዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታ ለማስተዳደር የሚያስችል የድርጅቱን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የራሱን የግንባታ መመሪያ ቢያወጣ በግንባታ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ለመቅረፍ ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

137. ድርጅቱ ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የካቲት 1999 ዓ/ም ያወጣው መመሪያ ላይ ያሉትን ክፍተቶች በማጥናት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኤሮኖቲካል ያልሆኑ ገቢዎች ለማስተዳደር የሚጠቀሙባቸውን የሌሎች አገሮች ተመኩሮ ከድርጅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር መመሪያውን ለማሻሻል የተጀመረው ጥናት ውስጥ እንዲካተት በማድረግ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ እንዲጸድቅ ቢያደርግ በነባሩ መመሪያ ክፍተት ምክንያት የሚፈጠሩ የአሰራር ችግሮች ለመቅረፍ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

138. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ እና የተሟላ የሰው ሃይል እንዲኖረው ቢደረግ በዘርፎቹ የሚከናወኑ ተግባራት ላይ የቁጥጥር እና የክትትል ሂደቱ የተሻለ እንዲሆን ይረዳል፡፡

139. ድርጅቱ ለሚያስገነባቸው ኤርፖርቶች ግንባታቸው ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ የአዋጪነት ጥናት /ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መልካአ ምድራዊ አቀማመጥ ወዘተ/ እንዲጠና ቢያደርግ ኤርፖርቶቹ ተገንብተው ሲጠናቀቁ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡና በአገሪቷ እድገትና ትራንስፎርሜሽ እድገት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

140. ድርጅቱ የሚያስተዳድራቸው ኤርፖርቶች የይዞታ በተሟላ መልኩ ማረጋገጫ ካርታ /Title Deed/፣ የመሬት አጠቃቀም ፕላን/Land use plan/ እና መሪ ዕቅድ/Master Plan/ እንዲኖራቸው ቢያደርግ የአጭር እና የረጅም ጊዜ የግንባታ ዕቅድ ለማውጣትና ኤርፖርቶችን በአግባቡ ለማስተዳዳር እገዛ ያደርጋል፡፡

141. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ ተገንብተው ሊጠናቀቁና ጊዜያዊ ርክክብ እንዲደረገላቸው ቢደረግ ድርጅቱ በየጊዜው በሚያሻቅቡ የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ንረት ምክንያት ከፍ የሚለው የግንባታ ወጪ ከመቀነሱ ባሻገር ግንባታዎቹ ተጠናቀው በወቅቱ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ይረዳል ፡፡

142. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ፣ በበቂ ጥናት የተመሰረተ ዲዛይን እንዲሰራላቸው እና የግንባታውን የቀን ተቀን ሂደት የሚቆጣጠር ባለሞያ እንዲመደብላቸው ቢደረግ ግንባታዎች ከተያዘላቸው የገንዘብ በጀት በላይ እንዳያስወጡ ያስችላል፡፡

143. ድርጅቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁ መሰረተ ልማቶች ጊዜያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኋላ የመጨረሻ ርክክብ ቢደረግና በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ህጋዊ እርምጃ ቢወስድ፣ በወቅቱ የግንባታዎችን ጥራት ከማስጠበቅና ውሉን ከማሰስከበር በተጨማሪ የመጨረሻ ርክክብ ባለመደረጉ ምክንያት ከራሱ ወጪ ግድፈቶችን ለማስተካከል የሚያወጣውን ያልተገባ ወጪ እንዳያወጣ ይረዳዋል፡፡

144. ድርጅቱ የሚገነባቸውና እያስገነባቸው ላሉ ኤርፖርቶች ቅድምያ ለደህንነት በመስጠት አስተማማኝ የዙሪያ አጥር፣ በለሊት የጥበቃ መብራቶች፣ በቂና ደረጃቸው የጠበቁ የጥበቃ ማማዎች፣ ደረጃቸውን የጠበቁና በቂ የፍተሻ ማሺኖች፣ ደረጃቸው የጠበቁ 360 ዲግሪ የኤርፖርቱን ክልል ሊያሳይ የሚችል የእሳት አደጋ የመመልከቻ ሰገነትና /Watchroom/ አስፈላጊ የእሳት አደጋ ግብአቶች፣ ማንኛውም አደጋ ሲከሰት በፍጥነት ለመድረስ የሚያስችል የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እና ኤርፖርቱን ለመጠበቅ የተሰማሩ የጥበቃ አካላት ምቹ የስራ አካባቢ ማለትም መኖሪያ ቤት፣ ውሃና መብራት በሚሟላት የአይሮፕላኖች፣ የመንገደኞችና የሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነት የተጠበቀ አስተማማኝና ቀልጣፋ የኤርፖርት አገልግሎት እንዲኖር ቢደረግ በሰው በንብረትና በሃገር ገፅታ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አስከፊ አደጋ ለመከላከል ያስችላል፡፡

145. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በግንባታው ኮንትራት ውሉ መሰረት /Specification/ ግንባታቸው እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር ቢደረግ የግንባታዎቹ ጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ያስችላል፡፡

146. በድርጅቱ የግዢ መመሪያ መሰረት የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድርበት ወቅት በቴክኒካል ብቃት እና በዋጋ መመዘኛ ላለፉት ተጫራቾች የድህረ ብቃት ግምገማ በማድረግ ያላቸውን ተጫራቾች በወቅቱ ያላቸው የግንባታ /ፕሮጀክት/ ብዛት ካላቸው የሰው ሀይል፣ ማቴርያልና የፋይናንስ አቅም ጋር በማነጻጸር እና መልካም ስም /**የበፊት አፈፃፀም**/ በጥልቀት በማየት አሸናፊውን እንዲለይ ቢደረግ በስራ ተቋራጮች እና በአማካሪ መሀንዲሶች ምክንያት የሚደርሰው የግንባታ የጥራት መጓደሎች፣ መዘግየቶች እና ከተያዘላቸው የኮንትራት ዋጋ በላይ የሚወጣውን ወጪ ለመቀነስ ይረዳል፡፡

147. በድርጅቱ የተገነቡ እና በመገንባት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች /ህንፃዎች/ በቂ የውሃ አቅርቦት እና ሙሉ ስርጭት እንዲኖራቸው ቢደረግ ለመንገደኞች እና በኤርፖርቱ ውስጥ ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት የተሟላ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ምቹ የስራ አካባቢን በመፍጠር ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

148. በድርጅቱ የተገነቡ ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር ከፍታ ያላቸው ህንጻዎች አሳንስሮች ያለማቋረጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ቢደረግ አካል ጉዳተኞችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከማድረግ በተጨማሪ መንገደኞች፣ ሰራተኞች እና ተከራዮች በሚያገኙትን አገልግሎት እንዲረኩ በማድረግ የድርጅቱን ገቢ ከፍ እንዲል ለማድረግ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

149. ድርጅቱ በሚያስገነባቸው መሰረተ ልማቶች ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በስራ ተቋራጮች እና በአማካሪ መሀንዲሶች ለሚደርሱ የስራ ጥራት ጉድለቶች ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሙሉ በሙሉ የታዩ ግድፈቶችን እንዲየስተካክሉ እና ጉድለቱን ያደረሱ አካላት በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ቢያደርግ ግንባታዎቹ ጥራት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ የህግ የበላይነትን በማስጠበቅ በሌሎች የድርጅቱ ግንባታዎች ላይ የጥራት መጓደሎች እንዳይከሰቱ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

150. ድርጅቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ቀጣይነት ያለው ዕቅድ በማውጣት ጥገናና ዕድሳት ቢደረግላቸው ለተጠቃሚ ምቹ እንዲሆኑ ከማድረግ በተጨማሪ በጥገናና እድሳት መዘግየት ምክንያት መሰረተ ልማቶቹ መስጠት ከነበረባቸው የአገልግሎት ዘመን በፊት እንዳይፈራርሱ፣ በሰውና በንብረት ላይ አደጋ እንዳያደርሱ እና የግንባታው ወጪ ከፍ እንዳይል ያስችላል፡፡

151. ኤሮኔቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ለመኪና ማቆሚያ በየሁለት ዓመት፣ ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረፅ ነፃ ሱቅ፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቅያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመት እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ ቢደረግ የድርጅቱ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እንዲል ከማድረጉ ባሻገር ለሌሎች በዚህ ንግድ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ዜጎች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ለመስጠት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

152. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ድርጅቱ ተከራይ የገባውን የውል ስምምነት ከጣሰ፣ ወይም የተከራየውን ይዞታ በንፅህና ካልያዘ፣ ወይም ተከራይ ውሉን ማቋረጥ ከፈለገ፣ ወይም ተመሳሳይ አሳማኝ ምክንያት በጽሑፍ ካቀረበ፣ ወይም ድርጅቱ ውል እንዲታደስ ለደንበኛው የውል እድሳት በጊዜ ገደብ አስታውቆ ምላሽ ካልሰጠው ወይም ተከራይ በ3 ወራት ውስጥ የሚፈለግበትን ኪራይ አጠናቆ ካልከፈለ፣ ወይም ደርጅቱ ይዞታውን ለሌላ ተግባር ከፈለገው በነበረው ውል መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን እንዲቋረጥ ቢያደርግ ህግን ከማስከበር ባሻገር የድርጅቱ ጥቅሞች እንዲከበሩና በአከራይና በተከራይ ያለው ግኑኝነት ጤናማና ስርአት ያለው እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

153. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች ትናንሽ መጋዘኖች እና ሁለት ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶላቸው ተጫራቾች ላልቀረቡላቸው የኪራይ ይዞታዎች በስተቀር ሌሎቹን የጨረታ ህጉን ተከትሎ በጋዜጣ በግልፅ ጨረታ እንዲከራዩ ቢደረግ ድርጅቱ ከኪራይ ቦታዎች አሁን በካ/ሜ ከሚያገው ገቢ በላይ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡

154. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት በድርድር የሚከራየው ቦታ በክልል ኤርፖርቶች ከሆነ ከስድስት ወራት እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ የኤርፖርት ሀላፊዎች በሚያቀርቡትን መነሻ ዋጋ መሰረት በማድረግ የድርድር ኮሚቴው ለተከራዩ ውል አዋውሎ ቦታው ከማስረከቡ በፊት ውሉ ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ እንዲፀድቅ ቢያደርግ በድርድር እንዲከራዩ የሚደረጉ የድርጅቱ የኪራይ ቦታዎች በትክክል ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶላቸው ተከራይ ያላገኙ ስለመሆናቸው ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

155. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ መኖሩ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ስለመኖሩን በማረጋገጥ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ በማጥናት ኪራይ እንዲጨመር ቢያደርግ የድርጅቱን ገቢ ከፍ ለማድረግና ለዕድሳትና ለጥገና የሚያወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን ያስችላል፡፡

156. ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውል በወቅቱ ተግባራዊ ቢያደርግ በአከራይና በተከራይ የሚፈጠውን አለመግባባት ከመቅረፉ በተጨማሪ ከኪራይ የሚያገኘውን ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እንዲልና በኤርፖርቶቹ ውስጥ ያለው የግብይት ሂደት /ስርዓት/ የተሻለ እንዲሆን በማድረግ የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ይረዳል፡፡

157. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት በብሔራዊ የአየር ፋስሊቴሽን ፕሮግራም ታህሳስ 2005 ዓ/ም በተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር መሰረት፡

- በኤርፖርቶቹ ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት አስፈላጊውን ፋሲሊቲዎች እና ለስራ ምቹ የሆኑ ቦታዎችን ቢያሟላ፣
- በኤርፖርት ውስጥ ለሚቀርቡ አገልግሎቶች ባለድርሻ አካላት በአለም አቀፍ ግዴታዎች እና ተመራጭ አሰራሮች መሰረት እንዲሰሩ ስርዓት በመዘርጋት አፈጻጸማቸዉ ላይ ክትትል ቢያደርግ፣

- በኤርፖርት ዉስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እና የቁጥጥር ስራ ለሚያከናውኑ ባለድርሻ አካላት ቢያስተባብር እንዲሁም
- በኤርፖርት ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞች የደንበኞች አያያዝ ስልጠና እንዲያገኙ ቢያደርግ በአህጉር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃ የተሻለ የኤርፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖረውና የደንበኞቹን ፍላጎት በማሟላት ገቢውን ከአመት አመት ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

ምስጋና

በኦዲቱ ወቅት መረጃ በማቅረብ፣ ለቃለመጠይቅ ፍቃደኛ በመሆን እና ቢሮና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች በማቅረብ ስራው ቀና እንዲሆን ለተደረገልን ትብብር ለድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ሃላፊዎች፣ ሠራተኞች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ከልብ እናመሰግናለን፡፡

አባሪዎች

አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

የኦዲቱ አቅጣጫ Audit Issue	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. ድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረት ልማት ግንባታና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደር በተመለከተ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ ምልኩ ለመወጣት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑንን መገምገም፡፡ 1.1ድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን በተመለከተ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችል ተገቢውን ያሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን ማረጋገጥ ፤	1. ድርጅቱ የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት እንዲያስችለው የመቋቋሚያ አዋጁና ደንቡ እንዲሻሻልለት ያጋጠሙትን ችግሮ በጥናት አስደግፎ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ ይገባል፡፡
	2. ድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታ ለማስተዳደር የሚያስችል የወጣውን ደንብ መሰረት በማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣና መመሪያውን ተግባራዊ ሊያደረገ ይገባል፡፡
	3. ድርጅቱ ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል የወጣውን ደንብ መሰረት በማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣና መመሪያውን ተግባራዊ ሊያደረገ ይገባል፡፡
1.2.ድርጅቱ የሚስገነባቸው ኤርፖርቶች በጥናት የተደገፉና ባነስተኛ ገንዘብና ጊዜ እንዲሁም በተገቢው የጥራት ደረጃ የተገነቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤	4. በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች በአዋጪነት ጥናት ላይ እንዲመሰረቱ እና በጥናቱ መሰረት አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	5. ድርጅቱ የሚያስተዳድራቸው ኤርፖርቶች መሪ ዕቅድ/Master Plan/ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	6. በክልሎችም ሆነ በአዲስ አበባ የተገነቡም ሆነ የሚገነቡ የማስፋፍያም ሆነ አዳዲስ ግንባታዎች የኤርፖርቱን መሪ ዕቅድ /Master Plan/ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡
	7. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ ተገንብተው ሊጠናቀቁና ግዚያዊ ርክክብ ሊደረግ ይገባል፡፡
	8. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው በጀት ተገንብተው ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡
	9. በግዚያዊ ርክክብ ወቅት በግንባታው ውል መሰረት ስራዎቹ ሙሉ በሙሉ ስለመሰራታቸው በሚመለከተው ባለ ሞያ መረጋገጥ አለበት፡፡
	10. ግንባታቸው የተጠናቀቁ መሰረተ ልማቶች ጊዚያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኋላ የመጨረሻ ርክክብ ሊደረግና በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ድርጅቱ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
	11. ድርጅቱ ለአይሮፕላኖች፣ ለመንገዶኞችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝና ቀልጣፋ የኤርፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማደረግ

	አለበት፡፡
	12. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በግንባታ ኮንትራት ውሉ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ መሰረት መግንባታቸው ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡
	13. ድርጅቱ የህንፃ ተቋራጮችና አማካሪዎች በጨረታ በሚያወዳድርበት ወቅት ያነሰ ዋጋ ያቀረበ ብቻ ከመምረጡ በፊት ያላቸው የማቴርያል፣የስው ሀይል፣ የፋይናንስ አቅም እና መልካም ስም /የበፊት አፈፃፀም/ ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገበዋል፡፡
	14. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች/ ህንፃዎች/ በቂ የውሃ አቅርቦት፣ ሙሉ ስርጭት እና ውሃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	15. ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር ከፍታ ያለው ማንኛውም ህንፃ አሳንሰር ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፡፡ አሳንስሮች ያለማቋረጥ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ ይኖሩባቸዋል፡፡
1.3ድርጅቱ ለሚያስገነባቸው ኤርፖርቶች የስራ አፈፃፀም ክትትል ፣ቁጥጥር ግምገማና ርክክብ የሚያደርግበት የአሰራር ስርአት የዘረጋ፣ተግባራዊ ያደረገና እንዲሁም በታዩት ልዩነቶች ላይ አስፈላዚው እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ማረጋገጥ፣	16. ማንኛውም የስራ ተቋራጭ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በሚገነባው ህንፃ ወይም የህንፃ አካል ላይ ለሚደርሰው የስራ ጥራት ጉድለት ተጠያቂነቱ ሳይቀር ጉድለቱን እንዲያስተካክል መደረግ አለበት፡፡
	17. ድርጅቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ሊኖረውና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ በማውጣት ጥገናና ዕድሳት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
	18. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ የሰው ሃይል ሊኖረው ይገባል፡፡
1.4ድርጅቱ የኤርፖርቶች ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ያከራይና ተከራይ ውል እና መመሪያ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡	19. ድርጅቱ ለመኪና ማቆሚያ በየሁለት ዓመት፤ ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረፅ ነፃ ሱቅ፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቅያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመት እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ ማድረግ አለበት፡፡
	20. ድረጅቱ ያከራያቸውን ነባር ይዞታዎች የውል ቆይታ ዘመን እስከሚያልቅ ድረስ በየዓመቱ የአገልግሎት እድሳት ማድረግ አለበት፡፡
	21. ድርጅቱ የኪራይ ውሉ ዘመን ሲያበቃ ተከራይ በኪራይ የተረከበውን ባዶ ቦታ ወድያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንዲመልስና እንዲያስረክብ ማድረግ አለበት፡፡
	22. ድርጅቱ ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች ትናንሽ መጋዘኖች እና ሁለት ግዜ የጨረታ ማስታወቅያ ወጥቶላቸው ተጨራቾች ላልቀረቡላቸው የኪራይ ይዞታዎች በስተቀር ሌሎቹን የጨረታ ህጉን ተከትሎ በጨረታ እንዲከራዩ ማድረግ አለበት፡፡
	23. በድርድር የሚከራየው ቦታ በክልል ኤርፖርቶች ከሆነ ከስድስት ወራት እስከ አንድ

	አመት ለሚሆን ጊዜ የኤርፖርት ሀላፊዎች የሚያቀርቡትን መነሻ መሰረት በማድረግ የድርድር ኮሚቴው ለተከራዩ ውል አዋውሎ ቦታው ከማስረከቡ በፊት ውሉ ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ ማስፀደቅ አለበት፡፡
	24. ድርጅቱ ተከራይ የገባውን የውል ስምምነት ከጣሰ፣ ወይም የተከራየውን ይዞታ በንፅህና ካልያዘ፣ ተከራይ ውሉን ማቋረጥ ከፈለገ፣ ተመሳሳይ አሳማኝ ምክንያት በጽሑፍ ካቀረበ፣ ድርጅቱ ውል እንዲታደስ ለደንበኛው የውል እድሳት በጊዜ ገደብ አስታውቆ ምላሽ ካልሰጠው፣ ተከራይ በ3 ወራት ውስጥ የሚፈለግበትን ኪራይ አጠናቆ ካልከፈለ፣ ወይም ደርጅቱ ይዞታውን ለሌላ ተግባር ከፈለገው በነበረው ውል መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡
	25. ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ መኖሩ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ከተደረገ በተመጣጣኝ በየዓመቱ ኪራይ መጨመር አለበት፡፡
	26. ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውልን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
	27. ድርጅቱ ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ የሰው ሃይል ሊኖረው ይገባል፡፡
2.ድርጅቱ የኤርፖርቶች ግናባታና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተገቢው ቅንጂታዊ የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡	28. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ 29. ድርጅቱ ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

አባሪ 2፡ በጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃ በተመለከተ

በጋምቤላ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንፃበፊት ለፊት ከበስተኋላ ላይ የሚገኙት ባለ 860 ሳ./ሜ ስፋት የአልሚኒየም በርና መስኮት /French Windows and Doors / ልኬታቸው ከውለታ ሠነዱና ከዲዛይኑ አንሶ ስለመገኘቱ የሚሳይ ሠንጠረጅ፡፡

On specification “Windows” Item No 7-8 and 7-9

ሠንጠረጅ 1

ተቁ	ውለታ ሰነዱና ዲዛይኑ ላይ የተመለከተው መጠን	ተገንብቶ የሚገኘው መጠን	
1	Type WD1 860 x 275 ሳሜ	855 x 238 ሳሜ	ከፊት ለፊት (በመግቢያ)
2	Type WD2 860 x 275 ሳሜ	840 x 232 ሳሜ	
3	Type WD3 860 x 275 ሳሜ	837 x 275 ሳሜ	
4	Type WD4 860 x 275 ሳሜ	866 x 275 ሳሜ	
5	Type WD5 860 x 275 ሳሜ	830 x 275 ሳሜ	ከጀርባ (በበረራ)
6	Type WD6 860 x 275 ሳሜ	850 x 275 ሳሜ	
7	Type WD7 860 x 275 ሳሜ	865x 275 ሳሜ	

አባሪ 3፡ ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን በተመለከተ

ከታች የተዘረዘሩት 15 የድርጅቱ ተከራዮች ከ1995 ዓ/ም እስከ 1998 ዓ/ም ከድርጅቱ ጋር ውል የፈጸሙ ቢሆንም የካቲት 1999 ዓ/ም ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ መሰረት በየአምስት ዓመት ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ መደረግ ሲገባቸው እስካሁን ድረስ በብቸኝነት በኤርፖርቱ እየነገዱ የሚገኙ ናቸው፡፡

- ለንደን ካፌና ሳተላይት ሬስቶራንት ፣ 109.9 ካ/ሜ በዓመት ብር 138 474፣ በግንቦት 1/1996 ዓ/ም የኪራይ ውል ዘመን፣
- በኮድ ቁጥር AACS 02 የይዞታዉ መጠን 54.0 ካሬ ሜትር፣የይዞታዉ ዓይነት ለህትመት ውጤቶች/Press shop/በተርሚናል ቁጥር 2፣የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት፣
- በኮድ ቁጥር AACS 07 የይዞታዉ መጠን 54.0 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለCultural Cusin በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 5,220.00 /አምስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ ብር/ በካሬ ሜትር በአመት
- በኮድ ቁጥር AACS 22 የይዞታዉ መጠን 12.0 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለሻንጣ ማሸጊያ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 4,100.00 /አራት ሺ አንድ መቶ ብር/ በካሬ ሜትር በአመት፣
- አልፋራጅ ትሬዲንግ ኃ/የተወሰነ የግልማህበር፡- የይዞታዉ መጠን በኮድ ቁጥር /AACS 13/ 631.0 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለቀረጥ ነፃ ሱቅ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣
- በኮድ ቁጥር AARS 12 የይዞታዉ መጠን 141.30 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለካውንተር ሰርቪስ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 4,100.00 /አራት ሺ አንድ መቶ ብር/ በካሬ ሜትር በአመት፣
- በኮድ ቁጥር AACS 09 የይዞታዉ መጠን 31.10 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለወርቅ ጌጣጌጥ/Gold Shop/ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣
- በኮድ ቁጥር AACS 21 የይዞታዉ መጠን 25.9 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለአበባ መሸጫ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 4,100.00 /አራት ሺ አንድ መቶ ብር/ በካሬ ሜትር በአመት፣
- ላሊበላ ወርቅ ቤት የይዞታዉ መጠን በኮድ ቁጥር /AACS 03 / 31.10 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለወርቅ ጌጣጌጥ/Gold Shop/ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣
- ሲቲ ቢዝነስ ኮምፒውተር የይዞታዉ መጠን በኮድ ቁጥር /AACS 04 / 104. 0 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለቢዝነስ ሴንተር በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣

- በኮድ ቁጥር AACS 06 የይዞታዉ መጠን 31.10 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለብር ጌጣጌጥ/Silver Shop/ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣
- ድሬ ኢንዱስትሪ ኃ/የተወሰነ የግልማህበር የይዞታዉ መጠን በኮድ ቁጥር /AACS 12 / 54.0 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለቆዳ ውጤቶች መሸጫ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣
- ሕይወት ለማ ትሬዲንግ የይዞታዉ መጠን በኮድ ቁጥር /AACS 05/ 31.10 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለሀገር ባህል ልብሶች መሸጫ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት ፣
- ሲማ ትሬዲንግ የይዞታዉ መጠን በኮድ ቁጥር /AACS 11 / 31.10 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለተቀረፁ ሙዚቃዎች መሸጫ በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት እና
- በኮድ ቁጥር /AACS 16 / የይዞታዉ መጠን 33.4 ካሬ ሜትር፣ የይዞታዉ ዓይነት ለሱፐር ማርኬት በተርሚናል ቁጥር 2፣ የክፍያ መጠን ብር 8,100.00 /ስምንት ሺ አንድ መቶ ብር /በካሬ ሜትር በአመት፡፡

አባሪ 4፡ ያለ ክፍያ ተከራዮች በተርሚናል አንድ እና ሁለት የሚጠቀሙበት የድርጅቱ ቦታ

ቀን 17/03/06ዓ/ም

በ09/03/06 ዓ/ም በተርሚናል አንድ /መናፈሻ/ በ02/07/05 ዓ/ም በተርሚናል ሁለት /ዲፓርቸር/ በሚገኙ ተከራዮች የተደረገ የመስክ ጉብኝት

1. ተርሚናል አንድ መናፈሻ

ተ.ቁ	የመለያ ቁጥር /የተከራዩ ስም/ (code no	የአገልግሎት አይነተት (types of servise)	በውሉ ላይ ያለ የኪራክ ቦታ በካ/ሜ Actual rent/sq.m A	በመስክ ጉብኝት ወቅት ሲለካ እየተገለገሉበት ያለ ጠቅላላ ቦታ በካ/ሜ Total area in use/sq.m B	ከውሉ ውጭ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚገለገሉበት ቦታ በካ/ሜ variationin sq.m C=B-A	የኪራይ ዋጋ በካ/ሜ Rental price/sq.m D	ከውሉ ውጭ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚገለገሉበት ቦታ በብር varation in birr E=C*D
1	CA-5 ውዱ ሁርይ	cafeteria	21.73	9.40*29= 272.6	250.87	1000.00	250,870.00
2	CA-3 Kahsay G/Hiwot	cafeteria Internet cafe	52.46+42.60 = 95.06	14.20*34.25=486.35	391.29	/1000.00 + 802.00 //2 = 901	352,552.29
3	CA-2 Girma Abezo	cafeteria	23.73	29.20 *13=379.6	355.87	1000.00	355,870.00
4	CA-1 Enanu Teshome	cafeteria	24.37	12.80*19= 243.2	218.83	1000.00	218,830.00
5	CA-4 Tigist Bekele & Birhanu Bekele	cafeteria	21.73	31.35*12.8= 401.28	379.55	1000.00	379,550.00
6	Wubalem Tadesse	cafeteria	21	13*19= 247	226	1000.00	226,000.00
				ጠቅላላ ድምር	1822.41		1,783,672.00

2. ተርሚናል ሁለት /ዲፓርቸር/

ተ.ቁ	የመለያ ቁጥር (code no)	የአገልግሎት አይነተት (types of servise)	በውሉ ያለ የኪራይ ቦታ/ኪ/ሜ/ስ Actual rent/sq.m	የኪራይ ተመን ብር /ኪ / ሜ /ስ በአመት Rental price/sq.m	ከውሉ ውጭ እተገለገሉበት የሚገኝ ቦታ በካ.ሜ	ከውሉ ውጭ እተገለገሉበት የሚገኝ ቦታ በብር
1.	AARS-07	Ethiopian hotel restaurant	100.69	5220.00	11.44	59,716.80
2.	AACS-07	-	58.72	8100	1.9	15,390.00
3.	AARS-01	Cultural cloth shop	62.40	21365.15	1.5	32,047.70
4.	AARS-02	The obelisk snak bar	260	5,220.00	17.78	92,811.60
5.	AACS-01	Ethiopian hand craft	108	8,100.00	/8.84 + 3.9 /=12.76	103,356.00
6.	AARS-11	London café & satalite restorant	180.40	4,100.00	/18.10*13.6=246.16/ - 180.4 = 65.76	269,616.00
7.	AARS-12	Selamawit alebachew Yellow spot	141.30	4,100.00	17.4*10.10= 175.74/ -141.30 =34.44	141,204.00
	ጠቅላላ ድምር				145.58	714,142 .10